# መርማሪ ኮሚሲዮን

ከውብሸት አየለ ጌጤ

2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# መርማሪ ኮሚሲዮን

ከውብሸት አየለ ጌጤ

woubaye@yahoo.com

## 1 መግቢያ

ይህ ጽሁፍ በ 1966 ዓም በየካቲቱ የ ኢትዮጵያ አብዮት ምክንያት በቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የነበሩትን ባለስልጣኖች ሥራቸውንና አገራቸውን በቅን ልቦናና በትክክል የማከናወን ግዴታቸውን በመዘንጋት ፤ያለ አገባብ በሥልጣናቸው የተጠቀሙና ታማኝነት የጎደላቸውን እንዲሁም በዳኝነትና በአስተዳደር በደል ያደረሱ ካሉ ፤ ተለይተው እንዲታወቁና በህግ እንዲቀጡ ለማድረግ፤ በዚህ ምርመራ እና ውጤትም ሕዝብ በመንግስት ላይ ያለው እምነት እንዲሰፋ ለማመቻቸት፤ በመጨረሻም በመንግስት ባለሥልጣኖችም ላይ ሊኖር የሚገባውን ታማኝነት ለማረጋገጥ እንዲቻል የሚል ግብ ይዞ በአዋጅ ቁጥር 326/66 ሰኔ 8 ቀን 1966ዓም የተቋቋመው መርማሪ ኮሚስዮን ተግባሩን በትክክል ተወጥቶ እንደሆነ መመርመር ነው።

ጽሁፉ አተኩሮ የመረመረውም ኮሚስዮኑ እንዲቋቋም ንጉሰነገሥቱ ትዕዛዝ ከሰጡበት ከመጋቢት 16 ቀን 1966 ዓም ጀምሮ ኮሚስዮኑ ተመርማሪዎቹ እንዲከሰሱ የሚያዘውን ውሳኔውን እና ዝርዝር ምርመራዎችን ለልዩ ጦር ፍርድ ቤት ጽህፈት ቤት እስከ አስረከበበት እስከ ህዳር 13 1967 እና ተመርማሪዎቹ ከህግ ውጭ እስከ ተገደሉበት እስከ ህዳር 14 1967 ቀን ድረስ ብቻ ነው።

በተጨማሪም ኮሚስዮኑ በራሱ አነሳሽነት በ1965 ዓም ከወሎ ረሃብ እና እልቂት ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል የመረመራቸውን ባለስልጣኖች በአዋጅ ቁጥር 326/66 ድንጋጌ መሰረት ስራውን መፈጸም አለመፈጸሙን አገናዝቦ ትዝብቱን አስፍሮአል።

በመጨረሻም ኮሚስዮኑ በህግ የተደነገገውን የስራ ዘመኑን ከተቋቋመበት አዋጅ አንጻር እንዴትና መቼ እንዳጠናቀቀ ይመለከታል።

## 2 የአመሰራረቱ ታሪካዊ ምክንያት እና አባላቱ

በ1966ቱ የ ኢትዮጵያ አብዮት ምክንያት የካቲት 20 ቀን 1966 ዓም የጸሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ ካቢኔ ለንጉሰነገሥቱ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ከሥልጣኑ ወረደ። በምትኩ ንጉሰ ነገሥቱ በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን የሚመራ አዲስ ካቢኔ እንዲቋቋም አዘዙ።

ህዝቡ የደረሰበትን በደል ምክንያት አድርጎ የጀመረውን አመጽ በአዲሱ ካቢኔም አላቋረጠም። ይህንን ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለማብረድ ፤እግረ መንገዱንም ህገወጥ በሆነ መንገድ የበለጸጉ የመንግስት ባለስልጣኖችም ካሉ የሚመረምር አንድ ጊዚያዊ መርማሪ ድርጅት ማቋቋም ያስፈልጋል ተብሎ በልጅ እንዳልካቸው መኮንን ካቢኔ ታመነ።[1]

ይህንኑ መሰረት በማድረግ ንጉሰ ነገሥቱም መጋቢት 16 ቀን 1966 ዓም፡- “የመንግሥት ሥራ በሐቀኝነት፤ በታማኝነት ና በትጋት መሥራት ስለአለበት ፤ኃላፊነት የተቀበሉ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሁሉ ይህን መንፈስ ተከትለው ሥራቸውን በጥንቃቄ ማከናወን የሚገባቸው መሆኑን በመገንዘብ ፤ንጹሁን የመንግሥት ባለሥልጣን ከጥፋተኛው መለየት ፤የመንግሥት ስም ለማስከበርና አጥፊ ሆኖ የተገኘው ወደ ፍርድ ሸንጎ እንዲመራ ለማድረግ ታስቦ፤ በአለፈው ጊዜ የነበሩትና አሁን በሥራ ላይ ያሉት የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ያፈሩት ሀብትና ያባከኑት የመንግሥት ንብረት ቢኖር ፤ተገቢውን ሕጋዊ ምርመራ ተከትሎ የሚያጣራ አንድ ኮሚሲዮን እንዲቋቋም” ብለው ንጉሳዊ ትዕዛዝ ሰጡ።

በትዕዛዙም መሰረት መጋቢት 19 ቀን 1966 ዓም ንጹሁን የመንግሥት ባለሥልጣን ከጥፋተኛው በመለየት ጥፋተኛውን የሚያስቀጣ ፤የመንግሥትን ሥም የሚያስከብር ፤በልጅ እንዳልካቸው መንግሥት የተሾሙ ሰባት አባላትን የያዘ መርማሪ ኮሚሲዮን ተቋቋመ ።[2]አባላቱም አቶ ጎሩይ ጥበቡ፣አቶ አበበ በንቲ፣ ፊታውራሪ ታደሰ ማርቆስ፣ኮሎኔል ኃይለማርያም አረዶ፣አቶ መዋዕለ ሙብራቱ፣ሻለቃ ሽመልስ መታፈርያ እና አቶ ቢልልኝ ማንደፍሮ ናቸው።[3]

እነዚህ ሰባት አባላት ለኮሚሲዮኑ ሕጋዊ አቋም የሚሰጠውን ረቂቅ ሕግ በ ስምንት ቀን አዘጋጅተው መጋቢት 27 ቀን 1966 ዓም ለወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አስረከቡ።[4] የወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ይህን የሕግ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቀረቡ።

---

[1] የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ4
[2] የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ
[3] ወንበር የዓለማየሁ ኃይሌ መታሰብያ ድርጅት ፔሮዲካል የ1966ቱ መርማሪ ኮሚስዮን አነሳስ ክንውን እና ከዝያ የቀመስነው ገጽ7 በዛወርቅ ሺመላሽ
[4] ዝኒ ከማሁ

የሚኒስትሮች ምክር ቤቱም በቀረበው የሕግ ረቂቅ ላይ ከመከረበት በኋላ ሚያዝያ 21 ቀን 1966 ዓም ለፓርላማ አስተላለፈ።[5]

ፓርላማውም በቀረበለት የኮሚሽዮን ማቋቋምያ ረቂቅ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ከመከረ በኋላ ተመርማሪው ወገን ሥራአስፈጻሚው የመንግሥት አካል በመሆኑ ምርመራው ወገናዊ እንዳይሆን፤ ስራውም በነጻነት እንዲሰራ መርማሪዎቹን ይህ አካል ሊመርጥ አይገባም የሚል ጥብቅ አቋም ወሰደ።[6]

በዚህም ምክንያት አስቀድመው በሥራ አስፈጻሚው ተመርጠው ረቂቅ ህጉን የአዘጋጁት ሰባት ሰዎች ሰኔ 7 ቀን 1966 ዓም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋ ቀርበው ተሰናበቱ።[7]ከዚሁ ጋር ተያይዞም ፓርላማው ፤ በቀረበለት ረቂቅ ላይ ዋና ዋና የተባሉ ሶስት ለውጦች አደረገ።

የመጀመርያው የፓርላማው ትኩረት፤ የአባላት አመራረጥ እና ብዛት ነበር። በዚህም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተረቀቀው ህግ አባላቱን አሥራ አንድ እንዲሆን ሲል ያቀረበውን ሃሳብ ፓርላማው አሥራ አምስት ይሁን ሲል ለወጠው።[8]

ሁለተኛው አቢይ ቁም ነገር በኮሚሽዮኑ አባላት የህብረተሰብ ውክልና ላይም ፓርላማው የተለየ አቋም ያዘ። በዚሁ መሰረትም 6 ሰዎች ብሄራዊ ምክር ቤቱ ከህብረተሰቡ ይመርጣል የሚል ድንጋጌ በአንቀጹ በማስፈር፣የኮሚሽዮኑን 40% አባላት የመምረጡን መብት ፓርላማው ለራሱ ወሰደ።[9]

እንዲሁም መለዮ ለባሹ በኮሚሽዮኑ ውስጥ ልክ እንደ ፓርላማው 6 አባላት ይኑሩት በማለት ሌላውን 40% የኮሚሽዮኑን አባላት ድርሻ ለመለዮ ለባሹ ሰጠ።

ቀሪውን 3 አባላት ማለትም 20% የሚሆነውን፡ ከኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አንድ ፤ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ከኢትዮጵያውያኑ መሃል አንድ ፤ ከዋናው ኦዲተር ሠራተኛ አንድ እንዲመደቡ ደነገገ።[10]

ብሄራዊ ምክር ቤቱ ከህብረተሰቡ መርጦ የኮሚሽዮኑ አባል ያደረጋቸው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርም ፤ ዶክተር በረከት ሀብተሥላሴ ፣ አምባሰደር ዘነበ ኃይሌ ፣ አቶ መዋእለ መብራቱ ጉግሳ ፣ አቶ ጅሃድ

[5] ዝኒ ከማሁ ገጽ9
[6] ዝኒ ከማሁገጽ9
[7] ዝኒ ከማሁ
[8] አዋጅ 326/66 አንቀጽ3 ንዑስ አንቀጽ2
[9] አዋጅ 326/66 አንቀጽ3 ንዑስ አንቀጽ2
[10]ዝኒ ከማሁ

አባቆያስ ቃዲ እና አቶ አሰፋ ሊበን [11] ናቸው። አምባሰደር ዘነበ ኃይሌ ምርጫውን ባለመቀበላቸው በምትካቸው አቶ ባሮ ቱምሳ ተመረጡ[12]።አቶ አሰፋ ሊበን በየትኛውም የኮሚስዮኑ ቃለጉባኤዎቹን በያዙት መዝገብም ሆነ በሪፖርቱ ላይ ስማቸው ተመዝግቦ አይገኝም።ከዚህ የተረዳሁት ይህን ኃላፊነት ያልተቀበሉ እና ስራውንም ያልሰሩ መሆኑን ነው።

በአዋጅ ቁጥር 326/66 ንዑስ አንቀ3 (2) ላይ በዝርዝር ከተቀመጡት የጦር ክፍሎች ተመድበው የኮሚስዮኑ አባል የሆኑት ኮማንደር ለማ ጉተማ ደበል ፣ ሌተና ኮለኔል ነጋሽ ወልደሚካኤል አብዲ፣ሌተና ኮለኔል ጌታሁን ዳምጤ ገብረየስ ፣ ሻለቃ ዓለማየሁ ሥዩም ወልደ ማርያም ፣ሻለቃ ምትኩ ደምሴ በየነ እና ሻለቃ ሠላም ጎሩይ ገሜ ናቸው።

ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ዶክተር መኮንን ወልደ አምላክ ወልደአረጋዊ ፤ከኦዲተር መ/ቤት አቶ ጌታቸው ደስታ ወልደሚካኤል፤ ከኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አቶ ሁሴን እስማኤል [13]የኮሚስዮኑ አባል ሆኑ።

እንቅስቃሴውን ህዝባዊ መልክ የሰጡትን ሰራተኞችን እና ማህበራቸውን እንዲሁም ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን እና ተማሪዎችን ይህ አዋጅ የመርማሪ ኮሚስዮኑ አባል አላደረጋቸውም።

እንዲሁም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ መምህራንን እና የመምህራን ማህበርን ዝቅተኛ በሆነ ቁጥር በኮሚስዮኑ እንዲወከሉ የኮሚስዮኑ መቋቋሚያ አዋጅ ደንግጓል።

በሌላ በኩል ድንጋጌው40% የኮሚስዮኑን አባላት ከመለዮ ለባሹ ማድረጉ የሚያስገነዝበው ፣ የወቅቱ ፓርላማ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሰራተኛው፣ከመምህራኑ ፣ ከሌሎቹ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ከተማሪዎች የመለዮ ለባሹን አቅም አጉልቶ በማየት ፣ የጦሩን ክፍል የጉዳዩ ባለቤት እንዳደረገው ይታያል።

ሦስተኛ ፓርላማው በሥራ ላይ ያሉት የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ያፈሩት ሀብትና ያባከኑት የመንግሥት ንብረት ቢኖር ፤ መመርመር ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም የአስተዳደር እና የዳኝነት በደልንም ኮሚስዮኑ የሚመረምረው ሌላው አብይ ጉዳይ እንዲሆን በመደንገግ የምርመራውን አድማስ አሰፋው።[14]

---

[11] ወንበር የዓለማየሁ ኃይሌ መታሰብያ ድርጅት ፔሮዲካል የ1966ቱ መርማሪ ኮሚስዮን አነሳስ ክንውን እና ከዝያ የቀመስነው ገጽ 8 በዛወርቅ ሺመላሽ

[12]ዝኒ ከማሁ

[13] መርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ 57 እና እንዘጭ እንቦጭ መስፍን ወ/ማርያም ገጽ125

[14]የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ11 እና አዋጅ 326/66 በአንቀጽ 3 ንኡስ አንቀጽ 2

በመጨረሻም በወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩት በክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ፊርማ፤ በንጉሰ ነገስቱ ዘመን በነበረው ፓርላማ ውሳኔ ሰኔ 8 ቀን 1966 ዓም የመርማሪ ኮሚሲዮን በአዋጅ ቁጥር 326/66 የተቋቋመ መሆኑን የሚገልጸው አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ወጣ።

የየካቲት ህዝባዊ አመጽን ለማብረድ ወይም አቅጣጫውን ለማስቀየር የተጠነሰሰው መርማሪ ኮሚስዮን የማቋቋም ጉዳይ ከወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር እጅ ወጥቶ ፓርላማ ሲደርስ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ህዝባዊ ጉልበት ያገኘ አስመስሎታል።

ይህም የፓርላማው ድካም ፕሮፌሰር መስፍን እንዳሉት "አስራ አምስት ከሚሆኑት የኮሚስዮኑ አባላት ውስጥ በትክክለኛነታቸው እና በኅሊናቸው ንጽህና ብርቅ የሆኑ ሰዎች"[15] ይዞም ይሁን ሳይዝ የተቋቋመ ስለመሆኑ የሚታይ እንዲሆን እርምጃውን ሁሉ በትኩረት ለመታዘብ ታሪክ ምእራፉን ሁሉ ክፍት አድርጎ ጠበቀው።

ኮሚስዮኑ ሐምሌ 9 ቀን 1966 ዓም ከአሥራ አምስት አባላቱ መካከል ዘጠኙ በመጀመርያ ቀርበው "ኮሚስዮኑን የፖለቲካ መሣርያ ላለማድረግ ፣ ብሔራዊና ሰብአዊ መብቶችን ለመጠበቅ፣ሥራቸውን በትክክለኝነት፣ በታማኝነት ያለአድልዎ ለማከናወን" የሚል ቃለ መሃላ ፈጽመው ሥራውን ጀመሩ።[16]ቃለ መሃላውም የተፈጸመው የጽህፈት ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር በነበሩት በአቶ ሰለሞን ገብረማርያም አስተናጋጅነት ንጉሰነገስቱ ዘንድ ቀርበው ነበር።[17]

ቃለ መሃላውም ከላይ እንደተገለጸው የኮሚስዮኑ አባላት ኮሚስዮኑን የፖለቲካ መሳርያ እንዳያደርጉት አጥብቆ ይከለክላል ፤ብሔራዊና ሰብአዊ መብቶችን አባላቱ እንዲጠብቁ ያስገድዳል ፤ሥራቸውን በትክክለኝነት በታማኝነትና ያለአድልዎ እንዲያከናውኑ እንደሚጠበቅ ከአዋጁ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል።[18]

እነዚህን ሦስት መሰረታዊ ሁኔታዎች አጉልቶ የያዘው የቃለ መሃላው ድንጋጌ እና ንጉሰ ነገሥቱ ፊት የተፈጸመው የቃለ መሃላው ሥርአት "በትክክለኛነታቸው እና በኅሊናቸው ንጽህና ብርቅ" የሆኑትን የኮሚስዮኑ አባላት አቅም ማጎልበት ይጠበቅበታል።

ኮሚስዮኑ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያምን ሊቀመንበር[19] አድርጎ ከመረጠ በኋላ አዋጁን በማጥናት ምርመራውን የሚያከናውንበት የምርመራ ሥነ ሥርአት አዘጋጀ ።[20]

---

[15] አገቱኒ ተምረን ወጣን ገጽ 12 መስፍን ወ/ማርያም አዲስ አበባ 2002

[16] የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ20

[17] አገቱኒ ተምረን ወጣን ገጽ11 መስፍን ወ/ማርያም አዲስ አበባ 2002

[18] አዋጁአዋጅ 326/66 አንቀጽ 4

ኮሚስዮኑ ጽህፈት ቤቱን በበላይነት የሚመሩ በአዋጁ አንቀጽ 4 (1) መሰረት ዋና ጸሐፊ የህግ ትምህርትና እውቀት ያላቸውን አቶ ሰይፉ ተከለማርያም ሀብቴን መድቧል።[21] እንዲሁም ኮሚስዮኑ አስራ አምስት ሰራተኞች ነበሩት፤ በተጨማሪም አስራ አራት የእድገት በሕብረት ዘማቾችም ተመድበውለት ነበር።[22]

## 3 የኮሚስዮኑ ምርመራ ና ውሳኔው

ኮሚስዮኑ በራሱ አነሳሽነት ወይም ከማንኛውም ሰው በሚቀርብ አቤቱታ ምርመራ መጀመር እንደሚችል አዋጁ ደንግጓል[23]። ሥራውንም የጀመረው ከወሎ ረሃብና እልቂት ጋር በተያያዘ የተፈጸመ የአስተዳደር በደልን የተመለከተ ነበር።ኮሚስዮኑ አብዛኛውን ምርመራ ያካሄደው አዲስ አበባ ከሚገኘው ጽ/ቤት ነበር።

ኮሚስዮኑ በራሱ አነሳሽነት ከጀመረው የ1965 ዓም ከወሎ ረሃብና ዕልቂትጋር ጉዳያቸው የተያያዘውን የ ባለስልጣኖችን ምርመራ ሲያካሂድ 138 ፋይሎችን፣87 ባለስልጣኖችን አስቀርቦ መርምሯል። ምርመራውን ከአጠናቀቀም በኋላ እነማን መከሰስ እንዳለባቸው ወሰነ።በዚሁ ውሳኔም በግልጽ የታየው ተመርማሪዎቹ ከ3 ወር እስከ አስር ዓመት ብቻ በእስር የሚያቆይ ክስ በ 1949 ዓም በወጣው ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 412 እና ቁጥር 509 እንዲመሰረት ያዘዘ መሆኑ ነው[24]።

በዚህ እልቂት ምክንያት በኃላፊነት ሊጠየቁ ይገባል ያላቸው 35 የቀድሞ ባለሥልጣኖች ናቸው።ከእነሱም ውስጥ ሁለቱ ጠ/ሚኒስትሮች ፣ሃያ ስድስቱ ሚኒስትሮች፣አንድ የክፍለካሀገር አስተዳዳሪ፣ ሶስት ሚኒስትር ደኤታዎች፣ሁለት ምክትል ሚኒስትሮች እና አንድ ሥራ አስኪያጅ ናቸው።[25]

የኮሚስዮ ውሳኔ ሁለት ገጽታ ያለው ነው። አንደኛው ገጽታ ባለስልጣኑ በግሉ የተጣለበትን ኃላፊነት አልተወጣም በሚል በግሉ ተጠያቂ የሚያደርግ ነው። ሁለተኛው የውሳኔው ሌላው ገጽታ የምኒስትሮች ምክር ቤቱን የሚመለከት ነው። ኮሚስዮኑ የምክር ቤትን ኃላፊነት አምስት መልክ ሰጥቶ፣ ምክርቤቱ ላልተወጣው ኃላፊነት የወቅቱን የምክር ቤት አባላት ተጠያቂ የሚያደርግ ነው።[26]

---

[19] ዝኒ ከማሁ

[20]የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ20

[21] መርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ 57 እና እንዘጭ እንቦጭ መስፍን ወ/ማርያም ገጽ

[22] መርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ 57እና58

[23] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 9(1)

[24] ደም ያዘለ ዶሴ የልዩ ዐቃቢ ሕግ ጽህፈት ቤት ገጽ182

[25] የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ26

[26] 34ኛ ዓመት ቁጥር555 አዲስ ዘመን ጋዜጣ ህዳር5 የወጣ

በዚሁ መሰረት በ1965 ዓም በወሎ ለደረሰው እልቂት በያዙት የመንግስት ኃላፊነት መሰረት ተገቢውን አላደረጉም፤ በሚገባም ኃላፊነታቸውን አልተወጡም ፤በማለት በግል ሊከሰሱ ይገባል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል።

ይህ ውሳኔ ያረፈባቸው ባለስልጣኖች የክፍለሃገሩ አስተዳዳሪ ክቡር ደጃዝማች ሰለሞን አብርሃ ፤ የእህል እጥረት አጥኚ ኮሚቴ አባል የነበሩት ክቡር ደጃዝማች ለገሰ በዙ፣ክቡር አቶ ሙላቱ ደበበ እና አቶ ጌታቸው በቀለ፤ ከማስታወቅያ ሚኒስቴር ክቡር ዶ/ር ተስፋዬ ገብረእግዚእ ፣ አቶ አበበ አንዱአለም፣ አቶ ንጉሴ ሐብተወልድ እና ክቡር አቶ ተገኝ የተሻወርቅ፤ከእርሻ ሚኒስቴር ክቡር አቶ አበበ ረታ፤ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ክቡር ጸሃፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ እና አቶ አብተው ዮሃንስ ናቸው።[27]

የውሳኔው ሌላው ገጽታ የምኒስትሮች ምክር ቤቱን የሚመለከተው ነው። ኮምሲዮኑ በዚሁ በ1965 ዓም በወሎ ለደረሰው አስከፊ ረሃብና መዘዙ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ህዝቡን ከደረሰበት አደጋ ሊታደገው ሲገባ ይህን የተጣለበትን ኃላፊነት አልተወጣም ሲል ወስኗል።ምክር ቤቱ የአልተወጣቸው ኃላፊነቶችም አምስት መልክ ያላቸው ጭብጦች መሆናቸውን በግልጽ ውሳኔው ላይ አስፍሯል።

የመጀመርያው ከህዳር 28 1961 ዓም እስከ ሐምሌ 18 1964 ዓም ድረስ የምኒስትሮች ምክር ቤት የረሃቡን ችግር ለማቃለል የሚያስችል ፕላን አውጥቶና ድርጅት አቋቁሞ ባለመስራቱ ቢዚህ ወቅት የምክር ቤቱ አባል የነበሩ ሁሉ በኃላፊነት ተጠይቂ ናቸው የሚል ነው።

በዚህ ውሳኔ መሰረት በጋራ ሊከሰሱ ይገባል ሲል ውሳኔውን ያሳረፈባቸው ፣ ክቡር ጸሃፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ክቡር ጸሃፊ ትዕዛዝ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ፣ ክቡር አቶ ይልማ ዴሬሳ ፣ ክቡር አቶ አበበ ረታ፣ክቡር አቶጌታሁን ተሰማ ፣ ክቡር አቶ አካለወርቅ ሀብተወልድ፣ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም፣ክቡር ቢትወደድ አስፍሃ ወ/ሚካኤል ፣ክቡር ደጃዝማች ግርማቸው ተ/ ሐዋርያት ፣ክቡር ቢትወደድ ዘውዴ ገ/ሕይወት፣ክቡር አቶ ታደሰ ያዕቆብ፣ ክቡር አቶ ማሞ ታደሰ፣ ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ ፣ ሻለቃ አሰፋ ለማ ፣ ክቡር ዶ/ር ሥዩም ሐረጎት ፣ ክቡር አቶ በለጠ ገ/ብረፃድቅ፣ ክቡር ዶ/ር ምናሴ ኃይሌ ፣ ክቡር አቶ ሣላ ሂኒት፣ ክቡር ደጃዝማች ክፍሌ እርገቱ፣ሌተና ጀነራል ከበደ ገብሬ፣ ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን፣ ክቡር አቶ ከተማ አበበ ፣ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመ ሥላሴ፣ ክቡር ፊታውራሪ አበበ ገብሬ ፣ ክቡር አቶ ሙላቱ ደበበ፣ክቡር ዶ/ር ተስፋዬ ገብረእግዚእ እና ክቡር አቶ በላይ አባይ ናቸው።[28]

---

[27] 34ኛ ዓመት ቁጥር555 አዲስ ዘመን ጋዜጣ ህዳር5 የወጣ

[28] 34ኛ ዓመት ቁጥር555 አዲስ ዘመን ጋዜጣ ህዳር5የወጣ

ሁለተኛው ውሳኔ ያረፈበት ጭብጥ የወሎ ክፍለሀገር አስተዳዳሪ የነበሩ በ1958ዓም የነበረውን ረሃብ ምክንያት አድርገው በክፍለሃገሩ የእህል ጎተራ እንዲሰራና ህዝቡ በፍቃዱ እህሉን አጠራቅሞ በችግር ቀን እራሱን እንዲረዳ ሃሳብ አቅርበው ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሃሳቡን ተቀብለው እንዲጠና አዘዙ። በትዕዛዙ መሰረትም ጥናቱ ተከናወነ።ምክርቤቱም ሊነጋገርበት አጀንዳ አድርጎ ያዘው።ለሁለት ዓመት ይህ ጥናት የምክርቤቱ አጀንዳ ሆኖ ከቆየ በኋላ ከአጀንደነት እንዲሰረዝ ተደረገ።በዚህ ምክንያት በጊዜው የነበሩት የምክር ቤቱ አባላት እንዲከሰሱ ወሰነ።

በዚህ ውሳኔ መሰረት በጋራ ሊከሰሱ ይገባል ሲል ውሳኔውን ያሳረፈባቸው ፤ ክቡር ጸሃፊ ትዕዛዝ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ፣ ክቡር አቶ አበበ ረታ፣ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም ፣ክቡር ቢትወደድ አስፍሃ ወ/ሚካኤል ፣ ክቡር አቶ ማሞ ታደሰ ፣ ሻለቃ አሰፋ ለማ ፣ዶ/ር ሥዩም ሐረጎት ፣ ክቡር አቶ በለጠ ገ/ብረፃድቅ ፣ ክቡር አቶ ሣላ ሂኒት እና ክቡር ዶ/ር ተስፋዬ ገብረእግዚአ ናቸው።[29]

ሶስተኛው ውሳኔ ያረፈበት ጭብጥ በ1964 ዓም በራያና ቆቦ አውራጃ ላይ ከደረሰው ድርቅ ጋር የተያያዘ ነው።የተራበውም ህዝብ ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ነበር። ለተራበው ሕዝብ በወቅቱ ምክር ቤቱ ስድሳ ሺህ ኩንታል ተጠይቆ ሳለ የላከው ሁለት ሺህ ኩንታል ብቻ በመሆኑ ፣በጊዜው የነበሩ አባላት በሙሉ ሊከሰሱ ይገባል ሲል ወሰነ።

በዚህ ውሳኔ መሰረት በጋራ ሊከሰሱ ይገባል ሲል ውሳኔውን ያሳረፈባቸው ፤ ክቡር ጸሃፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ክቡር አቶ አበበ ረታ፣ክቡር አቶ ጌታሁን ተሰማ ፣ ክቡር አቶ አካለወርቅ ሀብተወልድ፣ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም፣ ክቡር አቶ ታደሰ ያዕቆብ፣ክቡር አቶ ማሞ ታደሰ፣ ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ ፣ ክቡር ዶ/ር ሥዩም ሐረጎት፣ዶ/ር ምናሴ ኃይሌ፣ ክቡር አቶ ሣላ ሂኒት፣ሌተና ጀነራል ከበደ ገብሬ፣ ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን፣ ክቡር አቶ ከተማ አበበ ፣ክቡር አቶ ሙላቱ ደበበ እና ክቡር ዶ/ር ተስፋዬ ገብረዕግዚ ናቸው። [30]

አራተኛው ውሳኔ ያረፈበት ጭብጥ በ1964 ዓም የከረምቱ ወራት ድርቅ በወሎና በትግራይ ነበር። በዚህ ምክንያት በ1965 ዓም በእነዚህ ሁለት ክፍላተሃገር ረሃቡ ተባብሶ በተለይ የወሎ ህዝብ በእግሩ እየተሰደደ በጥርና በየካቲት ወራት በአዲስ አበባ አካባቢ መታየት ጀመረ። ይህ ሁኔታ ችግሩ እየተባባሰ ከባድ እልቂትን እስከሚያመጣ ድረስ በቂና አስቸኳይ እርምጃ ምክር ቤቱ አልወሰደም። በመሆኑም በዚህ ወቅት የነበሩት የምክርቤቱ አባላት ሁሉ በኃላፊነት ተጠይቂ ናቸው ሲል ወሰነ።

---

[29] 34ኛ ዓመት ቁጥር555 አዲስ ዘመን ጋዜጣ ህዳር5የወጣ

[30] 34ኛ ዓመት ቁጥር555 አዲስ ዘመን ጋዜጣ ህዳር5የወጣ

በዚህ ውሳኔ መሰረት በጋራ ሊከሰሱ ይገባል ሲል ውሳኔውን ያሳረፈባቸው ፤ ክቡር ጸሃፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ክቡር አቶ ጌታሁን ተሰማ ፣ ክቡር አቶ አካለወርቅ ሀብተወልድ ፣ ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም ፣ክቡር አቶ ታደሰ ያዕቆብ፣ ክቡር አቶ ማሞ ታደሰ ፣ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ ፣ዶ/ር ሥዩም ሐረጎት፣ ዶ/ር ምናሴ ኃይሌ ፣ክቡር አቶ ሣላ ሂኒት፣ ሌተና ጀነራል ከበደ ገብሬ፥ ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመ ሥላሴ፣ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን፣ክቡር አቶ ከተማ አበበ፣ ክቡር አቶ ሙላቱ ደበበ ፣ ክቡር ዶ/ር ተስፋዬ ገብረዕግዚእ ፣ክቡር አቶ በላይ አባይ እና ክቡር ደጃዝማች ካሣ ወልደማርያም ናቸው። [31]

አምስተኛው እና የመጨረሻው ጭብጥ በወሎ ክፍለሃገር በደረሰው ድርቅ ምክንያት በህዝቡ ላይ የችጋርና የረሃብ መጠን ከፍተኛ መሆኑን ከመጋቢት27 1965ዓም ጀምሮ ከተረዱ በኋላ ለችግረኞቹ እህል የሚገኝበትንና እንዲሁም የሚጓጓዝበትን ዘዴ ምክር ቤቱ የሚገባ እርምጃ አልወሰደም። በመሆኑም በዚህ ወቅት የምክርቤቱ አባላት የነበሩት ሁሉ በኃላፊነት ተጠይቂ ናቸው ሲል ወሰነ።

በዚህ ውሳኔ መሰረት በጋራ ሊከሰሱ ይገባል ሲል ውሳኔውን ያሳረፈባቸው ፤ ክቡር ጸሃፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ክቡር አቶጌታሁን ተሰማ ፣ ክቡር አቶ አካለወርቅ ሀብተወልድ ፣ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም ፣ ክቡር አቶ ታደሰ ያዕቆብ፣ክቡር አቶ ማሞ ታደሰ ፣ ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ ፣ ዶ/ር ሥዩም ሐረጎት ፣ዶ/ር ምናሴ ኃይሌ፥ክቡር አቶ ሣላ ሂኒት ፣ሌተና ጀነራል ከበደ ገብሬ፣ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመ ሥላሴ ፣ ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ፣ ክቡር አቶ ከተማ አበበ ፣ክቡር አቶ ሙላቱ ደበበ፣ክቡር ዶ/ር ተስፋዬ ገብረእግዚእ ፣ክቡር አቶ በላይ አባይ እና ክቡር ደጃዝማች ካሣ ወልደማርያም ናቸው።[32]

## 4 ኮሚስዮኑ እና ደርግ

የመርማሪ ኮሚስዮን አዋጅ እንዲረቀቅ ንጉሳዊ ትእዛዝ ከተሰጠበት ከመጋቢት 16 1966 ዓም ፤ አዋጁ እስከ ጸደቀበት ሰኔ 8 ቀን 1966 ዓም ድረስ መለዮ ለባሹን ወክሎ በአገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ የነበረው በኮሎኔል የዓለም ዘውድ ተሰማ ሊቀመንበርነት ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን ይመራ

[31] 34ኛ ዓመት ቁጥር555 አዲስ ዘመን ጋዜጣ ህዳር5የወጣ

[32] 34ኛ ዓመት ቁጥር555 አዲስ ዘመን ጋዜጣ ህዳር5የወጣ

የነበረው የጦር ኃይሎች ኮሚቴ በመባል የሚታወቀው ነበር።[33]ኮሚቴው የተቋቋመውም መጋቢት 1966ዓም ነው።

ኮሚቴው በአዲስ አበባ የሚገኙትን የጦር ክፍሎች እንወክላለን የሚሉ መስመራዊ መኮንኖችንና የበታች ሹማምንትን የያዘ ነበር።[34]ዋናው የዚህ ኮሚቴ ባለቤቶች እና ፈጣሪዎች የወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን እና የኮሚቴው ሊቀመንበር ኮሎኔል የዓለም ዘውድ ተሰማ የአየር ወለድ አዛዡ ነበሩ።[35] ዓላማውም የህዝቡን ጥያቄዎች መልስ ለማሰጠት የሚንቀሳቀስ በማስመሰል ተቀናቃኝ የመሆን አቅም ያላቸው እና የመሰላቸውንም በኃይል በቁጥጥር ስር ማድረግ ነው።

የሲቪል ባለስልጣኖች እና የጦር መኮንኖች ፣ የጸሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ ካቢኔ አባላትን ጨምሮ 24 የቀድሞ ባለስልጣኖች ሚያዝያ 18፣19፣22፣23 እና ግንቦት 23 ቀን 1966 ዓም[36] በንጉሰነገስቱ ፈቃድ የመታሰሩ እጣ ፈንታቸው የተጀመረው[37] ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን የጠቅላይ ሚንስትርነቱን ስልጣን በያዙ በሁለተኛ ወር ፤ የመርማሪ ኮሚስዮኑን የሚያቋቁመው ረቂቅ ህግ ለፓርላማው በቀረበ በወሩ ነው።

የእርምጃውም ዓላማ በቁጥጥር ስር የሚውሉትን እስረኞች በመርማሪ ኮሚሲዮን እያስመረመሩ ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን ለማቀዝቀዝ ፣ ለወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ፋታ በመስጠት ሥልጣኑን በቅጡ ለመቆጣጠር ነበር።

ይሁንና የሥራ አስፈጻሚው የመንግሥት አካል የኮሚስዮን አባላትን መምረጥ አይገባውም ሲል አስቀድሞ በልጅ እንዳልካቸው መንግሥት የተመረጡትን ሰባት የመርማሪ ኮሚስዮን አባላት ፓርላማው ባለመቀበሉ እና የኮሚሲዮኑንም ሕጋዊ አቋም የሚሰጠው የድንጋጌው ረቂቅ ለፓርላማው ከቀረበበት ከመጋቢት 27 ቀን 1966 ዓም እስከ ሰኔ 8 1966 ዓም ድረስ ሳይታወጅ በመቆየቱ ለወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ለልጅ እንዳልካቸው እንደታሰበው ኮሚስዮኑ ፋይዳ ያለው ጥቅም ሳይሰጥ ቀረ።

በተለምዶ ደርግ የሚባለው እና አገሪቱን ከመስከረም 2 ቀን 1967 ዓም ጀምሮ ለ 17 ዓመት የገዛው ወታደራዊ ተቋም በይፋ ራሱን ያስተዋወቀው ሰኔ 21 1966 ዓም ነው ።ይሀውም እነ ጸሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ ከታሰሩ ከሁለት ወር በኋላ የመርማሪ ኮሚሲዮን በአዋጅ ከተቋቋመ ከሁለት ሳምንት በኋላ መሆኑ ነበር።

---

[33] የኢትዮጵያ ታሪክ ከ 1847/1983 በፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ገጽ 241 እና ነበር ገጽ9
[34] ነበር ገጽ9
[35] ዝኒ ከማሁ
[36] የእስር ቤቱ አበሳ በታላቁ ቤተ መንግስት ገጽ180 እስከ 181 በአበራ ጀምበሬ
[37] የኢትዮጵያ ታሪክ ከ 1847/1983 በፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ገጽ 241

ደርግ ከተቋቋመበት ማግስት ጀምሮ የኮሎኔል የዓለም ዘውድ ተሰማ የጦር ኃይሎች ኮሚቴ ተበተነ። እሳቸውም ተሰወሩ።

ደርግም የኮሎኔል የዓለም ዘውድ ተሰማ የጦር ኃይሎች ኮሚቴን ሙሉ ለሙሉ ተክቶ ዕርምጃውንም በዚያው በተከፈተው መንገድ በሦስት ቀን ውስጥ አስር ከፍተኛ የንጉሰነገስቱ ሹማምንት አሰረ።በዚህም ምክንያት ሐምሌ 15/ 1966 ዓም ልጅ እንዳልካቸው መኮንንም ከሥልጣን ወርደው በንጉሰነገሥቱ ፈቃድ የመስዋዕት በግ አድርገው አቅርበዋቸው ከነበሩት የቀድሞ ባልደረቦቻቸው ጋር በሶስት ወራት ውስጥ ተቀላቅለው የአስተባባሪው ደርግ እስረኛ ሆኑ።[38]

ኮሎኔል የዓለም ዘውድ ተሰማም ተሰውረው ከነበሩበት የንጉሱን መውረድ ምክንያት አድርገው የደስታ መግለጫ ከላኩ በኋላ መስከረም 26 1967ዓም እጃቸውን ለደርግ ሰጡ ። እጣ ፈንታቸውም በእሳቸው በሚመራው የጦር ኃይሎች ኮሚቴ ከአሰራቸው ባለስልጣኖች ጋር ተቆራኝቶ አረፈው። [39]

መርማሪ ኮሚሲዮኑ በይፋ ሥራውን የጀመረው ሐምሌ 12ቀን 1966 ዓም[40] ፣ ደርግ አቅሙን አፈርጥሞ ፣ በህብረተሰብ ውስጥ ጎልቶ ወጥቶ ፣ጠቅላይ ሚኒስትር ማውረድ እና በምትኩም ሌላ መሾም በሚችልበት ወቅት ነው።

ይህንኑ አቅሙን መሰረት አድርጎ የኮሚስዮኑን ቢሮ ወደ አራተኛ ክፍለጦር አዞሮ በቅርበት ለመስራት ጥያቄ አቅርቧል። ለዚህ በኮለኔል መንግሥቱ በተደጋጋሚ ይቀርብ ለነበረው ጥያቄ ኮሚስዮኑ በአጀንዳነት ተወያይቶበት በአብዛኛው አባላት ውሳኔ ጥያቄው ውድቅ መደረጉን በፐሮፌሰር መስፍን ተገልጾአል።[41]

ደርግ የኮሚስዮኑን ሥራ ለመቆጣጠር ይቻለውም ዘንድ ሻለቃ መርሻ አድማሱን ከምድር ጦር፤ ኮማንደር ለማ ጉተማን ከባህር ኃይል መድቦ ነበር።[42]እንዲያውም ደርግ ሻለቃ መርሻ አድማሱን የኮሚስዮኑ ም/ሊቀመንበር አድርጎም ነበር የሾማቸው።ይሁንና የአየር ወለድ ጦር ክፍል እኒህን ሰው ሙሰኛ፣ ስስታም እና ጨቃኝ ናቸው በሚል ሹመቱንም ሆነ ምደባውን አምርሮ ስለተቃወመ የኮሚስዮኑ አባል ሳይሆኑ ቀረ። [43]

የኮማንደር ለማ ጉተማ የኮሚስዮኑ አባል እንዲሆኑ በደርግ የተደረገው ምደባ ተፈጻሚ ሆነ።[44]ከላይ እንደተገለጸው የሥራአስፈጻሚው የኮሚሲዮኑን አባላት እንዳይመርጥ ፓርላማው ያደረገው ክልከላ ዋጋ አጥቶ፤ የጦር ኃይሉ አባላት በአዋጁ በተቀመጠላቸው ኮታ መሰረት ከየክፍላቸው እንዲመርጡ

[38] የኢትዮጵያ ታሪክ ከ 1847/1983 በፐሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ገጽ 245
[39] ነበር ገጽ 89-90 ዘነበ ፈለቀ 1996
[40] ወንበር የዓለማየሁ ኃይሌ መታሰብያ ድርጅት ፔሮዲካል የ1966ቱ መርማሪ ኮሚስዮን አነሳስ ክንውን እና ከዝያ የቀመስነው ገጽ 8 በዛወርቅ
[41] አገቱኒ ተምረን ወጣን መስፍን ወ/ማርያምአዲስ ገጽ12 አዲስ አበባ 2002
[42] ነበር ገጽ52 ዘነበ ፈለቀ 1996
[43] ዝኒ ከማሁ
[44] ዝኒ ከማሁ

የተሰጣቸው መብት ተጥሶ ፤ደርግ የተባለው በወቅቱ ራሱን ለሥራ አስፈጻሚነት አደራጅቶ የሚንቀሳቀስ አካል ኮማንደሩን መደበ።

ኮሚስዮኑ በወሎ ረሃብ ምክንያት ለደረሰው እልቂት በኃላፊነት ሊጠየቁ ይገባል ባላቸው 35 የቀድሞ ባለሥልጣኖች ላይ የደረሰበትን ውሳኔ እና የተከሳሾችን ስም ዝርዝር ሕዳር4 ቀን 1967 በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አስታወቀ።[45]ይህም የኮምስዮኑ መግለጫ በማግስቱ ሕዳር 5 ቀን 1967 ዓም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ታትሞ በዝርዝር ወጣ።

ከላይ የተገለጸው ጋዜጣዊ መግለጫ ከተሰጠ ከአምስት ቀናት በኋላ ኮሚስዮኑ ህዳር 11 ቀን 1967 ዓም <u>ለልዩ ጦር ፍርድ ቤት የዐቃቢ ህግ ጽህፈት ቤት </u>በጻፈው ደብዳቤ ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ህዳር 6 ቀን 1967 ዓም በቁጥር አ/ደ/ቸ/6/2325 የተጻፈለትን አስታውሶ መልስ ሰጥቷል። በመልሱም በወሎ የደረሰውን ድርቅ እና ረሃብ እንዲሁም እልቂት በተመለከተ ባደረገው ምርመራ መሰረት፤ ከደብዳቤው አባሪ ጋር በተዘረዘሩት የመንግስት ባለስልጣናት ላይ ተለይቶ የተመለከተው የወንጀል ክስ እንዲቀርብባቸው አስታወቀ።[46]

እንደገና ከሁለት ቀን በኋላ ሕዳር 13 ቀን 1967 ዓም_እነዚህኑ ምርመራቸው ተጠናቅቋል የተባሉትን 35 ባለሥልጣኖች በተመለከተ የወንጀል ክስ እንዲቀርብባቸው ኮሚስዮኑ ሌላ ደብዳቤ <u>ለልዩ ጦር ፍርድ ቤቶች ጽህፈት ቤት</u> በመጻፍ የተከሳሾቹን ስም ዝርዝር አስተላለፈ።[47]

ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማርያም በዚሁ ሕዳር 13 1967 ዓም ለደርጉ ዘመቻና ጥበቃ መምርያ መኮንን "በጣም የሚያስቸኩል" የሚል ማሳሰብያ በላዩ ላይ በማስፈር ደብዳቤ ጽፈዋል።ይህ ደብዳቤ "ሰሞኑን የደርግ አባላት ባደረጉት ከፍተኛ ስብሰባ ፤ በአንደኛ ዙር የስም ዝርዝራቸው ከዚህ ጋር በተያያዘው የቀድሞ ባለስልጣናት ላይ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው በአንድ ድምጽ ወስነዋል" ይላል።

ይህ ለደርጉ ዘመቻና ጥበቃ መምርያ የተጻፈው የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማርያም ደብዳቤ ፤ ሌተና ጀነራል አማን ሚካኤል አንዶም በዚሁ ቀን እንዲያዙ ፤ እንዲሁም በከርቸሌ ግቢ ውስጥ ለ 54 ሰው መቀበርያ የሚሆን ጉድጓድ በዶዘር እንዲቆፈር ፣ በመጨረሻም ስማቸው ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው ሰነድ ላይ የተገለጹት54 የሲቪልና የጦር ባለስልጣናት ከምሽቱ ሁለት ሰአት ከእስረኞቹ

---

[45] የ መርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ 25

[46]ደም ያዘለ ዶሴ የልዩ ዐቃቢ ሕግ ጽህፈት ቤት ጥር 2002 ገጽ181—182

[47] የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ 26

ተለይተው ለብቻ እንዲቆዩና ከሌሊቱ 8 ሰአት ወደ ዋናው ከርቸሌ ተወስደው በጥይት ተደብድበው እንዲገደሉ የሚል ትእዛዝ የያዘ ነው።[48]

በዚህ ትዕዛዝ መሰረትም ህዳር 14 1967 ዓም ሌሊት ከኮሚስዮኑ ተመርማሪዎች መሃል በአስራ አንዱ ላይ እንዲሁም ወደፊት በሌላ ጭብጥ የኮሚስዮኑ ተመርማሪ ሊሆኑ በሚችሉ ሌሎች የንጉሰነገስቱ ዘመን ባለስልጣኖች ላይ የግፍ እርምጃ ተወስዶባቸዋል።

ከዚህ በላይ በተገለጸው ቀን በደርግ በግፍ የተገደሉት፣ ክቡር ጸሃፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን፣ሌተና ጀነራል ከበደ ገብሬ፣ ክቡር ዶ/ር ተስፋዬ ገብረእግዚእ፣ክቡር ደጃዝማች ሰለሞን አብርሃ፣ክቡር አቶ አካለወርቅ ሀብተወልድ፣ ክቡር አቶ ሙላቱ ደበበ ፣ክቡር ደጃዝማች ለገሰ በዙ ፣ክቡር ደጃዝማች ከፍሌ እርገቱ፣ ክቡር አቶ ተገኝ የተሻወርቅ እና ክቡር አቶ አበበ ረታ ናቸው።[49]

የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማርያምን ትእዛዝ እና የ ኮሚስዮኑን ውሳኔ የያዙት የሕዳር 13 ቀን 1967 ዓም እነዚህ ሁለት ደብዳቤዎች መገጣጠም አጋጣሚ ይሁን ወይም ሆን ተብሎ የተደረገ ስለመሆኑ ጥናት ሊደረግበት የሚገባ እንጅ በዝምታ ሊታለፍ ሕሊና የሚፈቅድ አይመስለኝም።

# 5 የኮሚስዮኑ የሥራ አፈጻጸም ከአዋጁ አንጻር

## 5.1 የአዋጁ ዓላማዎች

የመርማሪ ኮሚሲዮንን የአቋቋመው አዋጅ ቁጥር 326/66 በመግቢያው ላይ እንደአሰፈረው ዓላማው በንጉሰ ነገስቱ የተሾሙ ባለስልጣናት ሥራቸውን እና አገራቸውን በቅን ልቦና እና በትክክል የማከናወን ግዴታቸውን መፈጸም ወይም አለመፈጸማቸውን መመርመር ነበር።

ኮሚስዮኑ፣ አንድ ባለስልጣን ህገወጥ በሆነ መንገድ ያፈራው ሀብት፣ ያባከነውም የመንግስት ገንዘብ እና ንብረት ካለ እንዲሁም በዳኝነት እና በአስተዳደር ያደረሰው በደል ቢኖር የመመርመር ኃላፊነት አለበት። [50]እንዲሁም አዋጁ አጥፊ የሆኑት ተለይተው እንዲታወቁ እና ጥፋተኝነታቸው ሲረጋገጥ በህግ እንዲቀጡ የማድረግም ዓላማ አለው።

---

[48] የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሃብተወልድ ዜና መዋዕል ገጽ 244 መኮንን አብርሃ እናአብዮቱና ትዝታዬ ሌ/ኮሎኔል ፍስሐ ደስታ ገጽ130
[49] የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድቤት ም/ቁ/ል/0/ም/መ/ቁ/401/85 ገጽ7
[50] አዋጅ 326/66 አንቀጽ 8(1)

በመጨረሻም አዋጁ ሌላው በመግብያው የገለጻቸው ሊያስፈጽመው የሚገባቸው ሁለት አቢይ ጉዳዮች አሉ። እነሱም በመንግስት ላይ የህዝብ እምነት እንዲሰፋ ማድረግ እና የመንግስት ባለስልጣኖችም ሊኖራቸው የሚገባው ከፍተኛ ታማኝነት መኖር አስፈላጊ መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

5.2 ጠበቃ የመያዝ መብት

ምርመራውንም የሚያከናውነው በሚስጥር ፣አስፈላጊም ሲሆን በግልጽ ነው።[51] የመጀመርያ ደረጃ ምርመራ ሲካሄድ ወይም የአገር ጥቅም በተሻለ ሁኔታ ይጠበቃል በሚል አባላቱ ሲወስኑ፣ በሚስጥር ምርመራ ወይም በዝግ ምርመራውን ያከናውናሉ።የተጨበጠ ማስረጃ ሲገኝ ምርመራውን በግልጽ ወይም በክፍት ያደርጋል።ተመርማሪውም ጠበቃ ሊይዝ እንደሚችል ኮሚስዮኑ መፍቀድ እንዳለበት አዋጁ ይደነግጋል።[52]የ 1948 ዓም ሕገ መንግስት አንቀጽ 52 ይህንኑ ጠበቃ የመያዝ መብትን ደንግጓል።

የመርማሪ ኮሚሲዮንን የምርመራ ሂደት የያዙትን መዛግብት በኢትዮጵያ ጥናት እና ምርምር ተቋም ቤተመጻህፍት ውስጥ አግኝቼ መርምሬአለሁ።ከእነዚህ የምርመራ ሂደቱን ከያዙት መዛግብት የተረዳሁት ፣ ተመርማሪዎቹ ሕገ መንግስቱ እና የአዋጁ ድንጋጌ በሚፈቅደው መሰረት ጠበቃ ሳይዙ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ መልስ የሰጡ መሆኑን ነው።

ኮሚስዮኑ በእነዚህ የምርመራ መዝገቦች ላይ ይህን መብት ለተመርማሪዎቹ ማስገንዘቡን የሚያመለክት ምንም የተመዘገበ ነገር አይታይም። ምርመራው በሬድዮ ሲተላለፍም ምንም የጠበቃ ሚና አልተደመጠም።

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ተመርማሪው ጠበቃ ሊይዝ እንደሚችል የተደረገለትን የህግ ጥበቃ እና የከለላ መብት በኮምስዮኑ መነፈጉን ነው። ይህም ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ መብት ጥሰት በተመርማሪዎቹ ላይ ኮሚስዮኑ መፈጸሙን ያስረዳል።

5.3 መገናኛ ብዙሃንን ስለመጠቀም

ኮምሲዮኑ ፣ ማንኛውንም ባለስልጣን ወይም ሰው፣ በመሃላ በተደገፈ ጽሁፍ የራሱን እና የባለቤቱን እንዲሁም ከሌላ ሰው ጋር ያለውን የንብረት ግንኙነት ፣ የነበረውን ዋጋና ንብረቱ የሚገኝበትን ስፍራ፣ በዝርዝር እንዲገልጽ የመጠየቅ ሥልጣን አለው።[53]በተጨማሪም ኮምሲዮኑ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር

---

[51] ዝኒ ከማሁ 8(2)
[52] አዋጅ 326/66 አንቀጽ 8(2)
[53] አዋጅ 326/66 አንቀጽ 8(4)(ሀ)

ከ1933ዓም ወዲህ ከሚወስነው ጊዜ ጀምሮ ከማናቸውም ምንጭ የነበረውን ገቢና ገቢውን አስመልክቶ የተከፈለውን ማንኛውንም ግብር በዝርዝር እንዲገልጽ መጠየቅም ይችላል።[54]

አንድ ባለሥልጣን የንብረቱን ዋጋና ንብረቱ የሚገኝበትን ስፍራ ፣ ገቢና የገቢውን ልክ እና ገቢውን መሰረት አድርጎ የከፈለውን ማንኛውንም ግብር በዝርዝር እንዲገልጽ ተጠይቆ እምቢተኛ ከሆነ ፣ ኮምሲዮኑ ይህንኑ እምቢተኛነት በአዋጁ አንቀጽ 8(5) መሰረት ለህዝብ የማስታወቅ ስልጣን አለው።[55]

የኮምሲዮኑ አባላት ለህዝብ ጥቅም ነው ብለው ሲያምኑም፣ ተመርማሪው ከማናቸውም ምንጭ የነበረውን ገቢና በገቢው መሰረት የተከፈለውን ማንኛውንም ግብር_በተመለከተ የተሰጠን መግለጫ_አስመልክቶ ለህዝብ የማስታወቅ ስልጣን አለው።[56]

እንደሚታወቀው ኮምሲዮኑ ከተመርማሪዎቹ ጋር ያደርግ የነበረውን የምርመራ ሂደት በማስታወቂያ ሚኒስቴር ትብብር፣ በቴፐ እየተቀረጸ ለህዝቡ በሬድዮ እንዲሰማ አድርጓል።ይህንንም በማድረግ ዘላቂና ጠቃሚ ትምህርት ለሕዝብ ያተረፈ መሆኑንም ኮሚስዮኑ ያምንበታአል።[57]

በተጨማሪም ኮምስዮኑ ፣ምርመራውን በሬዲዮ ያስተላልፍ የነበረው፣ ምርመራው የሚያዳምጠው ህዝብ ለምርመራው የሚረዳ ጥቆማ እንዲሰጥ ለማበረታታት እና ለወደፊት የመንግስት ሰራተኞች ተጠያቂነት እና ኃላፊነት እንዳለባቸው ለማስገንዘብና ለማሰጠንቀቅ ስለመሆኑም ፕሮፌሰር መስፍን ገልጸዋል።[58]

ከህዝብ ለምርመራው የሚረዳ ጥቆማ ለማግኘትም ሆነ ፣ የመንግስት ሰራተኞችን ተጠያቂነት እና ኃላፊነት ለወደፊት ለማስገንዘብ እና ለማሰጠንቀቅ የኮምሲዮኑን ጥያቄ እና የተመርማሪዎቹን መልስ በሬድዮ እንዲተላለፍ የሚፈቅድ አንቀጽ ኮምስዮኑ ስራውን በሚያካሂድበት አዋጅ ቁጥር 326/66 አልተካተተም።

ከላይ በአዋጅ ቁጥር 326/66 አንቀጽ 8(5) ከተገለጸው የንብረት ጉዳይ ውጭ የምርመራውን ሂደትም በተለይ የኮሚስዮኑን ጥያቄ የተመርማሪዎቹንም ሆነ የአስረጅዎችን መልስ በሙሉም ይሁን ወይም በከፊል ለህዝብ የማስታወቅ ስልጣን ወይም በማናቸውም የመገናኛ ብዙሃን እንዲያስተላልፍ በአዋጁ ሥልጣኑ አልተሰጠውም።

ኮሚስዮኑን ያቋቋመው_አዋጅ ቁጥር 326/66 መሰረቱ በወቅቱ በሥራ ላይ የነበረው የ 1948 ዓም ሕገ መንግስት ነው።የዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 53፤ ባለሥልጣኖቹ የኮሚስዮኑ ተመርማሪዎች መሆናቸው

---

[54] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 8(4)(ለ)

[55] አዋጅ 326/66 አንቀጽ 8(4) (ሀ) እና (ለ)

[56] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 8(6) እና አንቀጽ 8(4) (ሀ) እና (ለ)

[57] የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ25

[58] እዘጭ እምቦጭ የኢትዮጵያ ጉዞ ገጽ125-126

ወይም በቁጥጥር ስር መገኘታቸው ይከሰሱ በተባለበት ወንጀል ሥልጣኑ የሆነ ፍርድ ቤት እስከሚያረጋግጥባቸው ድረስ ወንጀለኛ ተደርገው እንዳይታዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል።

የኮምሲዮኑ ጥያቄ እና የተመርማሪዎቹ መልስ በሬድዮ መተላለፉ የተመርማሪዎቹንም ከፍርድ በፊት ንጹህ ሆኖ በህግ ፊት የመታየት ሕገመንግስታዊ መብታቸውን ኮሚስዮኑ የምርመራውን ስራ እንደጀመረ ገና በጥዋቱ የጣሰው አቢይ ሕገወጥ ድርጊት ነበር። የዚህ ሕገወጥ ተግባር ያስከተለው ውጤትም ህዝቡ ተመርማሪዎቹን ከፍርድ ሂደት ውጭም ወንጀለኛ አድርጎ እንዲያያቸው ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድሯል።

ይህም የሚያስገነዝበን በመገናኛ ብዙሃን በተለይ በሬድዮ ከፍተኛ አጽንኦት ሰጥቶ የኮምሲዮኑ የማዋከብ ጥያቄ እና የተመርማሪዎቹ የተሸማቀቀ ፣ አንዳንዴም በእንባ በመታናቅ ይሰጡ የነበረው መልስ ይተላለፍ የነበረው ከህግ ውጭ መሆኑን ነው።

ኮሚስዮኑ የተቋቋመበትን ህግ ሳይጥስ፣የመርማሪዎቹን ጥያቄ እና የተመርማሪዎቹን መልስ በሬድዮ ሳያስተላልፍ፤ ኮሚስዮኑ ግልጽ የሆነ መግለጫ በወቅቱ በነበሩት ጋዜጦች፣ ራድዮ እና ቴሌቭዥን በተደጋጋሚ በማሰራጨት ጥቆማ እንዲቀርብለት ህብረተሰቡን ማበረታት ይችል ነበር።

አዋጁ በደነገገው መሰረት ምርመራው ተካሂዶ ፣ በምርመራው መሰረት ሊከሰሱ የሚገባቸው አዋጁ ሥልጣን በሰጣቸው ፍርድ ቤቶች ክስ ተመስርቶባቸው፣ እነሱም የመሰማት መብታቸው ተጠብቆ ተከራክረው ጥፋታቸው በመጨረሻው ፍርድ ቤት ሲወሰን ፣ ያኔ የምርመራውንም አካሄድ ሆነ ፍርዱን በአደባባይ በማውጣት ፣ የመንግስት ሰራተኞችን ተጠያቂነትንም ሆነ ኃላፊነትን ለወደፊት ለማስገንዘብ ይቻል ነበር።

ምርመራቸው በሬድዮ የተላለፈባቸው ተመርማሪዎች የደረሰባቸው የግፍ እርምጃ በግልጽ እየታወቀ፣ ከ አርባ ዓመት በኋላ ከህዝብ ለምርመራው የሚረዳ ጥቆማ ለማግኘት እና የመንግስት ሰራተኞችን ተጠያቂነት እና ኃላፊነት ለወደፊት ለማስገንዘብም ነው ምርመራውን እናስተላልፍ የነበረው ብሎ ዛሬ መመጻደቅ በሰው ቁስል እንጨት መስደድ ነው።

የኮምሲዮኑ የማዋከብ ጥያቄ እና የተመርማሪዎቹ የተሸማቀቀ መልስ ፣መርማሪዎቹን በተለይ ቀደም ቀደም ይሉ የነበሩትን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን እና ዶ/ር በረከት ሀብተስላሴን ህዝባዊ ደፋር እና ጀግና ሲያስመስል፣ ተመርማሪዎቹን በተቃራኒው በጭፍን በዳዮች አድርጎ አሳይቷል። በጊዜው የነበረውን ህዝባዊ ስሜት ሆን ብሎ ያጋጋለ እና ያባባሰ ፣የቀድሞ ባለሥልጣኖችን በጅምላ እንዲናቁ እና እንዲጠሉ ያደረገ ተግባር ነበር።

ከዚህ በላይ የተገለጸውን ገጽታ የያዘው የምርመራው አካሄድ በሬድዮ መተላለፉ ህዝባዊ አመጹን በየቀኑ በተጋጋለ ሁኔታ ለማሰቀጠል የሚያስችል የፕሮፖጋንዳ ጠቀሜታ እንዲኖረው አድርጓል።ይህም በወቅቱ የነበረውን የአብዮቱን ሂደት እንዲጧጧፍ የበኩሉን ፈጽሟል።

በአዋጁ ያልተፈቀደለትን የኮምሲዮኑን ጥያቄ እና የተመርማሪዎቹ መልስ በመገናኛ ብዙሃን በተለይ በሬድዮ እንዲተላለፍ መደረጉ የምርመራው አካሄድ የፖለቲካ ፍጀታ እዲኖረው አድርጓል። በዚህም ምክንያት አባላቱ ሰብአዊ መብቶችን የመጠበቅ ግዴታቸውን አልተወጡም፤ ስራቸውንም በትክክል እና ያለ አድልዎ ማከናወን አልቻሉም።

የኮሚስዮኑ አባላት ኮሚስዮኑን የግል ፖለቲካ አስተሳሰባቸውን ማስፈጸሚያ መሳርያ አድርገውታል። ብሄራዊ እና ሰብአዊ መብቶችን የመጠበቅ ግዴታ ያለበቸው ስለመሆኑ፣ ስራቸውን በትክክለኛነት ያለ አድልዎ ማከናወን እንዳለባቸው[59] ፣ማቋቋምያ አዋጁ አስገዳጅ ድንጋጌ የደነገገው ኮሚሲዮኑን እና አባላቱን ከዚህ አስከፊ ጥፋት ለማዳን ነበር።ይሁንና የምርመራው አካሄድ የህዝብን ስሜት ለፖለቲካ ጠቀሜታ እንዲያነሳሳ በማድረግ፣ የኮሚስዮኑ አባላት በአዋጁ ተወስኖ የተሰጣቸውን ስልጣን በማን አለብኝነት ጥሰዋል።

የሕዳር 14 1967 ዓም አረመናዊ ጭፍጨፋ ለደርግ ዘመን የጭካኔ ድርጊቶች የመጀመርያ ምዕራፍ ነው ። የኮሚስዮኑ ምርመራ በሬድዮ እንዲተላለፍ ማድረጉ ለዚህ አስከፊ ድርጊት ምንም አስተዋጽ አልነበረውም ለማለት መቻሉን እርግጠኛ መሆን አልቻልኩም።

## <u>5.4 ለተመርማሪዎቹ ጥበቃ ማድረግ</u>

ምርመራው የተጀመረ ባለስልጣን ምርመራው በጅምር እያለ እና ስለመከሰስ ወይም አለመከሰሱ ከመወሰኑ በፊት ከአገር ሊወጣ አይችልም።[60]ይሁን እና ምርመራው ያላለቀለት ባለስልጣን ለመንግስት ስራ ወይም አስገዳጅ በሆነ ምክንያት ከአገር መውጣት ካለበት፣ ኮሚሲዮኑ በቂ ነው የሚለውን ዋስትና አስቀድሞ እንዲሰጥ ከአደረገ በኋላ ተመርማሪው እንዲሄድ መፍቀድ ይችላል።[61]በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ተመርማሪው ለአስቸኳይ የመንግስት ሥራ ወደ ውጭ አገር መሄድ ከአለበት የኮሚሲዮኑ ፈቃድ ሳይጠየቅ ባለስልጣኑ ወደ ውጭ አገር ሊሄድ ይችላል።[62]

---

[59]አዋጅ 326/66 አንቀጽ 5
[60] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 9(2)
[61] ዝኒ ከማሁ
[62] አዋጅ 326/66 አንቀጽ 9(3)

በአዋጁ አንቀጽ 9 በተደነገጉት በእነዚህ ሶስት ንዑስ አንቀጾች ተመርማሪው እንኳን ዋስትና የተነፈገው እስረኛ ሊሆን ቀርቶ ካለው ኃላፊነት ላይ መነሳት ያለበት መሆኑን አይደነግግም።እንዲያውም ተመርማሪው ለኮሚስዮኑ ቃሉን የሚሰጠው በስራ ገበታው ላይ እያለ ሊሆን እንደሚችል ነው ከድንጋጌዎቹ መረዳት የሚቻለው።

እንደሚታወቀው ፓርላማው ኮሚስዮኑን በሚያቋቁመው አዋጅ ላይ ገና እየመከረ እያለ ነው ለምርመራው የተጋለጡት ባለስልጣናት የታሰሩት። ፓርላማው ይህን ሁኔታ እያወቀ ነው ከዚህ በላይ ያለውን የተመርማሪውን ነጻነት የማይገድብ ድንጋጌ አስፍሮ የሚገኘው።ፓርላማው ለተመርማሪው ይህን ሁሉ ጥበቃ የሚያደርገው ኮሚስዮኑ የተመርማሪውን መብት አጥብቆ ተገንዝቦ፣ የስራ አፈጻጸሙን በድንጋጌው መሰረት በማከናወን የህግ የበላይነት ሳይጣስ ምርመራውን እንዲያከናወን ለማድረግ ነበር።

አዋጁ እስከዚህ ድረስ ጥበቃ የሚያደርግላቸው የመርማሪ ኮሚስዮኑ ተመርማሪዎች፣ ምርመራቸው በጅምር እያለ እና ስለመከሰስ ወይም አለመከሰሳቸው ሳይወሰን ፣ ጥፋታቸው ስልጣኑ በሆነው ፍርድ ቤት ሳይረጋገጥባቸው ፤ እጃቸው በሰንሰለት እየታሰረ ከኮሚስዮኑ ፊት መቅረባቸው እና ምርመራው መከናወኑ አግባብ አልነበረም።እንዲሁም ባለስልጣናቱ እጃቸው በሰንሰለት እንደታሰረ ወደ ኮሚስዮኑ አዳራሽ ሲገቡ እና ሲወጡ ኃላፊነት የጎደላቸው ሰዎች ሰድበዋቸዋል፤ አፌዘውባቸዋል፤ ኮሚስዮኑ ይህን ክልከላ የማድረግ አቅሙ ነበረው ፤ይሁንና ከለላ አላደረገላቸውም።[63]

<u>5.5 የጸሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ ምርመራ</u>

በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የመርማሪ ኮሚስዮኑን የውሳኔና የምርመራዎቹን ቃለጉባኤዎች የያዙ IESMS የመለያ ቁጥሩ 1945 ፤ 1946፤ 1947፤ 1948 አራት ጥራዞች ይገኛሉ።

የመለያ ቁጥሩ 1945 የያዘው የምርመራ ቃለጉባኤ ከ 11ኛ-20ኛ ፤ የመለያ ቁጥሩ 1946 የያዘው የምርመራ ቃለጉባኤ ከ 27ኛ-36ኛ፤መለያ ቁጥሩ 1947 የያዘው የምርመራ ቃለጉባኤ ከ 37ኛ-53ኛ ድረስ ነው።

በእነዚህ በሶስት ጥራዞች ተለይተው የተያዙ ቃለጉባኤዎች ከነሃሴ 24 ቀን 1966ዓም እስከሰኔ 18 ቀን 1967 ድረስ ነው። ከእነዚህ የምርመራ ሂደቱን እና ውሳኔዎችን ከያዙት መዛግብት ያየሁትና ሌላው ያስደነገጠኝ ጉዳይ የጸሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ የምርመራ ሂደት ነው።

ጸሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ እንደሌሎቹ ተመርማሪዎች በተጠረጠሩበት ጉዳይ ምርመራቸውን የሚያስረዳ የኮምሲዮኑን ጥያቄ እና የእሳቸውን መልስ የያዘ የምርመራ ቃለጉባኤ ከምርመራ መዝገቡ

---

[63] የእስር ቤቱ አበሳ በታላቁ ቤተ መንግስት ከ 1966 እስከ 1974 በአበራ ጀምበሬ ገጽ 42

ውስጥ የለም። ከእኚህ ሰው ጉዳይ ጋር ተያይዞ መዝገቡ ውስጥ ያለው ፤ጥቅምት 25 ቀን 1967 ዓም በ30 ኛው ጉባኤ ላይ በግላቸው ሊከሰሱ ይገባል ወይስ አይገባም በሚል፣ የኮሚስዮኑ አባላት ክርክር ማድረጋቸውና ውሳኔ ላይ ሳይደርሱ መቅረታቸው ነው።[64] እንዲሁም ጥቅምት 27 ቀን 1967 ዓም በ32ኛው ጉባኤ ላይ አንደኛ ተከሳሽ ፤ በጠቅላይ ሚኒስትርነታቸው ጸሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድን፣ ሁለተኛ ተከሳሽ የካቢኔውን አባላት አድርጎ ኮሚስዮኑ የተጠያቂነት ውሳኔ መስጠቱ ይታያል።[65]

በአዋጁ መሰረት፤ መርማሪ ኮሚሲዮን ለተመርማሪው ጥያቄ ሳያቀርብ ፤ ተመርማሪውም በመሃላ ስር ሆኖ መልስ ሳይሰጥ ፤ በተለይ በነበራቸው ሥልጣን መሰረት በግል ኃላፊነታቸውን አልተወጡም ተብለው ሊከሰሱ ይገባል ወይም አይገባም የሚል ውሳኔ መስጠት ኮሚሲዮኑ አይቻለውም።

ጸሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ ከረጅሙ የፖለቲካ ገድላቸው የተወሰነውን ነሐሴ 6 ቀን 1966 ዓም በታይፕ ጽፈው ለኮሚሲዮኑ መስከረም 10 ቀን 1967 ዓም አቅርበዋል ተብሎ በሰፊው የሚነገርለት 88 ገጽ ኤፎር(A4) ጽሁፋቸውም ከመዝገቡ ጋር አልተያያዘም።ይህም ጽሁፍ ሊከሰሱ ይገባል ከተባሉበት በወሎ ከደረሰው ረሃብ ጋር በተያያዘ የቀረበም መከላከያ አይደለም ።ኮምሲዮኑ ጋ መስከረም 10 ቀን 1967 ዓም ቀርበው በመሃላ ቃላቸውን ሰጥተዋል።በወቅቱም በኮሚሲዮኑ የቀረቡላቸው አፋጣጭ ጥያቄዎችም በሬድዮ ተላልፈዋል።[66]

ይህ የፖለቲካ ፍጆታ እንዲኖሮው ተደርጎ በሊቀመንበሩ ፕሮፌስር መስፍን ወልደማርያም እና በዶክተር በረከት ሀብተሥላሴ የቀረቡት የወከባ እና የማሸማቀቅያ ጥያቄዎች እና ጸሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ የሰጡት መልሶች አልተመዘገቡም።ከመዝገቡ ውስጥ ይህም እንኳን አይገኝም።ይህም ኮሚስዮኑ ምን ያህል ስራውን ከህግ ውጭ ጥንቃቄ በጎደለው መልክ ያከናውን እንደነበር ያስረዳል።

## 5.6 በኮሚስዮኑ ውሳኔ መሰረት ክሱን የሚመሰርተው ተቋም

በ1948 ዓም ሕገ መንግስት አንቀጽ 75 ላይ የተገለጹት ባለስልጣኖች ማለትም በሚኒስትሮች እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ከሥራቸውና ከኃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ ክስ የሚመሰረትባቸው በንጉሰነገሥቱ ትዕዛዝ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው።

የመርማሪ ኮሚሲዮን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 326/66ም ይህንኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌ ተከትሎ ሚኒስትሮች እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኮሚስዮኑ እንዲከሰሱ ሲወስን ይህ የክስ ውሳኔ በንጉሰ ነገሥቱ ትእዛዝ

---

[64] የመርማሪ ኮሚስዮን ቃለ ጉባኤ27— 36 ገጽ 18-22 IESMS መለያ ቁጥር 1946

[65] የመርማሪ ኮሚስዮን ቃለ ጉባኤ27— 36 ገጽ 6 IESMS መለያ ቁጥር 1946

[66] የእስር ቤቱ አበሳ በታላቁ ቤተ መንግስት ገጽ42 በአበራ ጀምበሬ

እንደቀረበ ተቆጥሮ ክሱ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ አዋጁ ይደነግጋል።[67] ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የወንጀል ወይም የፍትሐብሄር ክሶችን የማየት ልዩ ስልጣን አለው።[68]

የፍርድ ሚኒስቴርም በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቀርቡ ክሶችን አይተው የሚወስኑ ጠቅላይ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዩ ችሎቶች የመመደብ ስልጣን በግልጽ ተሰጥቶታል።[69]

ምንም እንኳን በግልጽ የተቀመጠ ድንጋጌ ባይኖርም የጠቅላይ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዩ ችሎቶችን የመመደብ ስልጣን ያለው የፍርድ ሚኒስቴር የልዩ አቃቤ ህግ ጽህፈት ቤትንም የማቋቋም ወይም የመመደብ ሥልጣን አለው ብሎ መቀበል አግባብ ነው። ኮሚሲዮኑ ባደረገው ምርመራ መሰረት፤አንድ ባለስልጣን ወይም ሰው በሕግ ተጠያቂ ሆኖ ሲያገኘው የወንጀል ወይም የፍትሐብሄር ክስ እንዲቀርብ ያዛል። [70]

ይህን ክስ የመመስረት ሥልጣን ያለው  መሥርያ ቤት የሚሆነው የልዩ አቃቤ ህግ ጽህፈት ቤት ነው።[71] በዚህም ምክንያት በጠቅላይ እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዩ ችሎቶች ለሚታዩ የወንጀል ክሶች ልዩ አቃቤ ህግ ባለቤት ነው።

ይህ በእንዲህ እንደለ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 1/67 የዳኝነትና የአስተዳደር በደል ፤እንዲሁም ያለአግባብ መበልጸግ ወንጀል የፈጸሙ ባለሥልጣኖችን ክስ የሚያይ የጦር ፍርድ ቤት ይቋቋማል ቢልም በአገሪቱ ያሉ ፍርድ ቤቶች ሁሉ የተለመደ ሥራቸውን ይሰራሉ የሚል ድንጋጌም አለው።[72]

ልዩ ጦር ፍርድ ቤት የተቋቋመው በአዋጅ ቁጥር 7/67 ህዳር 7 ቀን 1967 ዓም በወጣ ነጋሪት ጋዜጣ ነው። አዋጁም ከጥቅምት ጀምሮ የሚጸና መሆኑ ተደንግጓል።

ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግም በአዋጅ ቁጥር 8/67 ህዳር 7 ቀን 1967 ዓም በወጣ ነጋሪት ጋዜጣ ታወጀ። የተፈጻሚነቱ ወሰን በልዩ ጦር ፍርድ ቤቶች በሚቀርቡ ሰዎች ላይ ሁሉ ላለፈውም ለወደፊቱም የሚጸና ነው።

---

67 አዋጅ 326/66   አንቀጽ 11 (1)
68 አዋጅ 326/66 አንቀጽ 11 (2)
69 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 11 (3)
70 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 10
71 አገቱኒ ተምረን ወጣን ገጽ12 መስፍን ወ/ማርያምአዲስ አበባ 2002
72 አዋጅ ቁጥር 1/67አንቀጽ11(7) ና (9)

ከዚህ በላይ የተገለጹት የልዩ ጦር ፍርድ ቤቶችንና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግን የደነገጉ የደርግ አዋጆች የምርመራ ኮሚሲዮኑ የተቋቋመበትን ልዩ ታሪካዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ አስገብተው ግልጽ በሆነ ድንጋጌ በመርማሪ ኮሚስዮን አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጾች (1)(2) እና (3) ላይ በምርመራው ውጤት መሰረት የሚቀርቡትን ክሶች አይተው የሚወስኑት የጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዩ ችሎቶች መሆናቸውን የሚያዘውን ድንጋጌ በግልጽ አልሰረዙም ፤ ወይም አላሻሻሉም።እንዲሁም የምርመራው ውጤትም በልዩ ጦር ፍርድ ቤቶች መታየት አለበት የሚል አስገዳጅ አንቀጽ በግልጽ አላሰፈሩም።

የምርመራ ኮሚሲዮኑን ያቋቋመው አዋጅ በፓርላማው ሲረቀቅ በዳኝነትና በአስተዳደር የተፈጸሙ በደሎችን የመመርመር ሥልጣን ለኮሚስዮኑ እንዲሰጠው አጥብቀው ከጠየቁት የህብረተሰብ ክፍሎች አንዱ የጦር ኃይሎች የፖሊስና የብሄራዊ ጦር አሰተባባሪ ደርግ አንዱ መሆኑን የኮምሲዮኑ ሪፖርት ይገልጻል።[73]

ከላይ እንደተገለጸው ኮሚስዮኑ በንጉሰ ነገስቱ ፓርላማ ይቋቋም እንጅ ቃለ መሃላ ፈጽሞሥራውንም በይፋ የጀመረው ደርግ ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓም መቋቋሙን ይፋ ከአደረገ ከሦስት ሳምንት በኋላ ሐምሌ 12 ቀን 1966 ዓም ነው።[74]

ደርግ መንግስት ከሆነበት ከመስከረም 2 1967 ዓም በኋላም ቢሆን ለመርማሪ ኮሚሲዮን ድጋፉን አልነፈገውም፤ ከላይ እንደተገለጸውም ከኮምስዮኑ ጋር ለመስራት አጥብቆ ጠይቋል።የፈረሰውም በደርግ መንግስት ዘመን ውስጥ የሁለት ዓመት ዕድሜ አስቆጥሮ ነው።

ይህም ማለት ደርግ እንደ ፓርላማው አልበተነውም ወይም እንደ 1948 ዓም ህገ መንግስትም አላገደውም፤ ወይም ከፍተኛው የሕገ መንግሥት ጉባኤ አራት ወራት ደክሞ ለህዝብ ውይይት እንደአቀረበው ረቂቅ ሕገ መንግስት አውቆ በማንአለብኝነት ለህዝብ እንዳይደርስ በማፈን ዋጋ ቢስ አላደረገውም።[75]

ወታደራዊው መንግሥት ከሚያወጣቸው አዋጆች ጋር መስመር ለመያዝ የሚያስችለው በ1967 ዓም (በ የትኛው ወር እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም) "አዲስና የተሻሻለ የመርማሪ ኮሚስዮን አዋጅ ረቂቅ" በራሱ በኮሚስዮኑ ተዘጋጅቶ ለርዕሰ ብሄሩ የቀረበውንም[76] ቢሆን ወታደራዊ መንግሥት ተቀብሎ ኮሚሲዮኑ የተቋቋመበትን አዋጅ ቁጥር 326/66ን አላሻሻለውም።

[73] የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ6
[74] የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ
[75] የሕይወቴ ታሪክ ተክለፃድቅ መኩርያ አዲስ አበባ 2008 ገጽ 274
[76] የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ43

ኮሚስዮኑ ይህን ረቂቅ ማዘጋጀቱ የሚያስረዳው፣ ራሱ በልዩ ሁኔታ እና ህግ የተቋቋመ መሆኑን በመገንዘብ ወታደራዊው መንግሥት ከሚያወጣቸው አዋጆች ጋር መስመር ለመያዝ የሚያስችል አዲስ ወይም የተሻሻለ ህግ ሳይወጣ ኮሚሲዮኑ ከተቋቋመበት እና ሥራውን ከሚመራበት አዋጅ ቁጥር 326/66 ውጭ አንድ ስንዝር መሄድ እንደማይችል የሚያውቅ መሆኑን ነው።

ይኸው አስተባባሪ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደርግ ተብሎ የመንግሥቱን ሥልጣን ሲይዝም ኮሚሲዮኑ የተቋቋመበትን ልዩ ሁኔታ የተቀበለው ለመሆኑ እነዚህ በቂ ማስረጃዎች ናቸው።

በመሆኑም በልዩ ታሪካዊ ሁኔታ በተደነገገው የመርማሪ ኮሚስዮን ማቋቋምያ ላይ ያሉ አንቀጾች በልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በአዋጅ ቁጥር 8/67 በግልጽ ስለአልተተኩ የተመርማሪዎቹ ጉዳይ በኮሚስዮኑ ማቋቋምያ አዋጅ ብቻ ነው መታየት የሚገባው።

ከላይ እንደተገለጸው ልዩ ጦር ፍርድ ቤትን የሚያቋቁመው አዋጅ ቁጥር 7/67 በነጋሪት ጋዜጣ የወጣው ህዳር 7 ቀን 1967 ዓም ነው።

ይህ ልዩ የጦር ፍርድ ቤት አቃቤ ህግን እና የልዩ የጦር ፍርድ ቤቶች ጽህፈት ቤትን የሚያቋቁመው አዋጅ በወጣ አራት እና ሰባት ቀናት ውስጥ እነዚህ ሁለት ተቋማት አሉ ፤ሥራቸውን ጀምረዋል ፤ብሎ ኮሚስዮኑ ተቀብሎ ና አምኖ ከላይ እንደተገለጸው የምርመራውን ውጤት ህዳር 11 ቀን 1967 ዓም በተጻፈ ደብዳቤ ለልዩ ጦር ፍርድ ቤት የዐቃቢ ህግ ጽህፈት ቤት ፣ እንደገና ሕዳር 13 ቀን 1967 ዓም ለልዩ ጦር ፍርድ ቤቶች ጽህፈት ቤት እንዴት ነው ሊልክ የሚችለው? በእነዚህ ተቋማት ስም የተጻፉትን እነዚህን ሁለት የኮሚስዮኑን ውሳኔዎች የተረከበው ማን ነው? ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው እላለሁ።

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም አገቱኒ ተምረን ወጣን በሚለው መጽሃፋቸው ገጽ12 ላይም፡ "የመርማሪ ኮሚስዮን ተግባር ክሶችንና ጉዳዮችን እየመረመረ ያስከስሳል ወይም አያስከስስም ብሎ ለልዩ አቃቤ ህግ (ሰረዙ የእኔ ነው) ማስተላለፍ ብቻ ነበር ፤ከዚህ በላይ የሆነ ኃላፊነትም ተግባርም አልነበረውም" ሲሉ ብለዋል።ይሁንና ኮሚስዮኑ የደረሰበትን ውጤት ያስተላለፈው በገለጻቸው ላይ እንደአስገነዘቡን ለልዩ አቃቤ ህግ ሳይሆን ለልዩ ጦር ፍርድ ቤት አቃቤ ህግ እና ለልዩ ጦር ፍርድ ቤቶች ጽህፈት ቤት ነው።

ኮሚሲዮኑ ሊያደርግ ይገባ የነበረው የምርመራ ኮሚሲዮኑ የተቋቋመበትን ልዩ ታሪካዊ እና ህጋዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተግባሩ እና ስልጣኑም ከተቋቋመበት አዋጅ የመነጨ መሆኑን መሰረት በማድረግ፤

እንዲሁም ኮሚስዮኑ ተመርማሪዎቹ ከ ሦስት ወር እስከ አስር ዓመት ብቻ በእስር የሚያቆይ ክስ በ 1949 ዓም በወጣው ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 412 እና ቁጥር 509 እንዲመሰረት ያዘዘ በመሆኑ[77]፤

በተጨማሪም በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የታወጁት የልዩ ጦር ፍርድ ቤቱም ሆነ የልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አዋጆች የምርመራ ኮሚሲዮኑን አሰራር በሚመለከት በግልጽ ኮምስዮኑ በተቋቋመበት አዋጅ ላይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች የሚለውጡ ምንም አዲስ ድንጋጌዎች ስለአልያዙ፤

የፍርድ ሚኒስቴርም በኮሚስዮኑ ማቋቋምያ አዋጅ መሰረት በኮምስዮኑ ምርመራ ውጤት አማካኝነት የሚቀርቡ ክሶችን አይተው የሚወስኑ የጠቅላይ ንጉሰ ነገሥት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዩ ችሎቶች የመመደብ ስልጣኑ በግልጽ ያልተሻረ በመሆኑ እና ተቋሙም በሙሉ ኃይሉ በወቅቱ ይሰራ ስለነበር፤

የተመርማሪዎችን ጉዳይ ለልዩ ጦር ፍርድ ቤት ልዩ አቃቤ ህግ ጽ/ቤት እና ለልዩ ጦር ፍርድ ቤቶች ጽህፈት ቤት እንድልክ አልገደድም የሚል አቋም ኮሚስዮኑ መውሰድ ነበረበት። ይሁንና አባላቱ ይህንን ጉዳይ ጭብጥ አድርገውም አልተወያዩበትም ፤ ወይም የተወያዩ ስለመሆኑ ሪፖርቱ ላይም ሆነ የምርመራዎችን ቃለ ጉባኤዎችን በያዙት መዝገቦችም ላይ የተመዘገበ ነገር የለም።

ይህም ባለመሆኑ ኮምሲዮኑ ህግ የመተርጎም መብት ሳይኖረው ህግ እንደተረጎመ ይታያል።ይህ ደግሞ እርምጃውን ህገወጥ ያደርገዋል።

5.7 የኮሚስዮኑ አባላት ገለልተኛነት

የአዋጁ አንቀጽ5 የኮሚስዮኑ አባላት ኮሚስዮኑን የፖለቲካ መሳርያ እንዳያደርጉት፣ ብሄራዊና ሰብአዊ መብቶችን መጠበቅ እንዳለባቸው፣ በታማኝነት እና ያለአድልዎ ስራቸውን እንዲሰሩ አጥብቆ ደንግጓል። ይህን ድንጋጌ አባላቱ ሊያከብሩት የሚችሉት በንጉሰ ነገሥቱ አገዛዝ ላይ አስቀድመው ያልፈረዱ እና ያልታገሉት እንዲሁም ለሥልጣን ከቋመጠው አምባገነኑ ደርግ ጋር ምንም ግኑኝነት ካልነበራቸው ብቻ ነው።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የአፄ ኃይለሥላሴን አገዛዝ ሲተቹ የቆዩ ከመሆኑም በላይ እራሳቸው አገቱኒ ተምረን ወጣን በሚለው መጽሃፋቸው ገጽ 11 ላይ እንዳስነበቡን አአስቀድመው በአገዛዙ ላይ ፈርደውበታል።መርማሪ ኮሚስዮን ምርመራውን በአከናወነበት  የወሎ ረሃብና እልቂቱን ጉዳይ በተመለከተም በወቅቱ ህዝቡን ለመታደግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረጋቸው ይታወቃል።የምርመራውን ሥራ በገለልተኛነት ለመሥራት አስቀድሞ በዚህ ጭብጥ ምንም አይነት አቋም ያለመውሰድ ኃላፊነቱን

[77] ደም ያዘለ ዶሴ የልዩ ዐቃቢ ሕግ ጽህፈት ቤት ገጽ182

በገለልተኛነት እና በንጹህ ህሊና ለመስራት አቅም ይሰጣል። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በሥርአቱ ላይ አስቀድመው የፈረዱ በመሆኑ የመርማሪ ኮሚስዮን አባል መሆን አይገባቸውም ነበር፤ ይሁኑም ከተባለ የወሎ ረሃብና እልቂቱን ከማንም በፊት ለማጋለጥ ከፍተኛ ስራ የሰሩ በመሆኑ ምስክር መሆን የሚገባቸው ሰው ናቸው። ስለዚህም አስቀድመው አቋም በያዙበት እና በታገሉት ጉዳይ ላይ መርማሪ መሆናቸው በንጹህ ህሊና የመሥራቱ ጉዳይ የሚታሰብ አይሆንም።ስለዚህም ምርመራውን ሊያከናውኑም ሆነ ውሳኔም ሊሰጡ አይችሉም። ምርጫውን መቀበላቸው የመጀመርያው የግዴለሽነት እርምጃቸው ነው።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም የኮሚስዮኑ ሊቀመንበር የነበሩት እስከ ጥቅምት 25/1967ዓም [78]ስድሳውቹ ሊገደሉ 19 ቀን እስኪቀር ድረስ ነበር።ከኮሚስዮኑ ሊቀመንበርነት የለቀቁት በራሳቸው ፈቃድ ነው።[79]ይህንን የኃለፊነት ቦታ ዶ/ር በረከት ሀብተ ሥላሴ ይፈልጉት ስለነበር እሳቸው ቦታውን እንዳይዙት ከቀሩት የኮሚስዮኑ አባላት ጋር በመሆን በደርግ ለኮሚስዮኑ የተመደቡትን ኮማንደር ለማ ጉተማን የኮሚስዮኑ ሊቀመንበር እንዲሆኑ የዛሬው ሰብአዊ መብት ተሟጋች አጥብቀው እንደሰሩ እና ድልም አድርገው ኮማንደሩን የኮሚስዮኑ ሁለተኛ ሊቀመንበር እንደአደሩጉአቸው በኩራት ገልጸውልናል። [80]ኮማንደር ለማ ጉተማ በግልጽ የ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማርያም የፖለቲካ ጓድ መሆናቸውንም የሚያሳየው በስርአቱ ውስጥ የመርማሪ ኮሚስዮኑን ስራ ከአጠናቀቁ በኋላ የያዝዋቸው ስልጣኖች በግልጽ ይመሰክራሉ።ኃላፊነቶቹም የጡረታ ኮምሽን ኮሚሽነር፤በሶማሊያ መንግስት ወረራ ወቅት የሐረርጌ ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ ፤የአገር ውስጥ አስተዳደር ሚኒስትር፤የኢሰፓኮ ዋና ጸሀፊ፤ የኢሰፓ ዋና ጸሀፊ፤በጀርመን ዴሞክራቲክ ሪፑብሊክ አምባሰደር፤ የስርአቱ የመጨረሻው ብሄራዊ ሸንጎ ም/ፕሬዚዳንት ነበሩ።ይህም ሁኔታ ሊያስገነዝበን የሚችለው ፤ አብዛኛው የኮሚስዮኑ አባላት ሻብያ ከተባለ መሰሪና አረመኔ ድርጅት ይልቅ ደርግ ለተባለው ግብዝና አረመኔ ያደሉ መሆኑን እና የራሳቸውንም ሆነ የኮሚስዮኑን ነጻነት ያቀዳጁበት ሥራ አለመስራታቸውን ነው።

ህዳር 14 1967 የቀድሞ ባለስልጣኖች በግፍ ከተገደሉ በኋላ አብዮቱም እየተጋጋለ ሲሄድ፤ የኮሚስዮኑ ዋነኛ ተዋናይ ዶክተር በረከት ሀብተ ሥላሴ ሻቢያን በግልጽ መቀላቀላቸው ኮሚሲዮኑ ገና ከጅምሩ ቢያንስ የሻብያ የፖለቲካ ጉዳይ የማስፈጸሚያ መድረክ እንደነበር ያሳያል።ሌላው ከዚህ የምንማረው ኮሚስዮኑ በተዘዋዋሪ ለሻብያ፣ በቀጥታ ደግሞ ለደርግ ጉዳይ አስፈጻሚነት የተጋለጠ መሆኑን ነው።

አምባሰደር ዘነበ ኃይሌ ምርጫውን ባለመቀበላቸው በምትካቸው በፓርላማው የተመረጡት አቶ ባሮ ቱምሳ የንጉሰ ነገሥቱን መንግስት በመቃወም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ በ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የነበራቸው ፣ ከደርግ ጋር ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ይሰራ የነበረውን ኢጭአት በመባል የሚታወቀውን የፖለቲካ ድርጅት የአቋቋሙና የመሩ፣የሕዝብ ድርጅት ጉዳዮች ጊዚያዊ ጽ/ቤት በደርግ

[78]የመርማሪ ኮሚስዮን ቃለ ጉባኤ ጥቅምት 25 1967 ገጽ2

[79] አገቱኒ ተምረን ወጣን መስፍን ወ/ማርያምአዲስ ገጽ12 አዲስ አበባ 2002

[80] አገቱኒ ተምረን ወጣን መስፍን ወ/ማርያምአዲስ ገጽ12 አዲስ አበባ 2002

የመጀመርያዎቹ ዘመን ለአባልነት ተመርጠው የአደራጁ፣[81]እንዲሁም አነግ የተባለውን ነጻ አውጭ የፓለቲካ ድርጅት መስራችና ግንባር ቀደም መሪ የነበሩ ፣እንዲህ ባለ ገለልተኛነትን በከፍተኛ ደረጃ በሚጠብቅ ኃላፊነት መካፈላቸው ጉዳዩን ለቆሙለት የፓለቲካ ግብ አላጋለጠውም ማለት አይቻልም።በመሆኑም ገለልተኛ የመሆኑ ጉዳይ እኒህን ሰውም በተመለከተ አደጋ ላይ ወድቆ ይታያል።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው አዋጁ እንዲከበር የደነገገው የአባላት የገለልተኛነት ስነምግባር ተፈጻሚ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚያመቻች አቅም አንድ አንድ የኮሚስዮኑ አባላት ያልነበራቸው መሆኑን ነው። ተወደደም ተጠላ ቃለ መሃላው ተጥሷል። ስለዚህም አገርን ለመታደግ በህይወት ያሉት የኮሚስዮኑ አባላት ስለራሳቸውና በህይወት ዛሬ ስለሌሉት ሁሉ ንስሃ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

<u>5.8 የኮሚስዮኑ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት</u>

ኮሚስዮኑ የምርመራዎቹን አካሄድና ውጤቱን  የሚያስያ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ለንጉሰነገሥቱ ለፓርላማው እና ለህዝቡ ማቅረብ እንዳለበት የአዋጁ አንቀጽ 8 ንውስ አንቀጽ(11)ደንግጓል።

ከላይ እንደተገለጸው ኮሚስዮኑ ሥራውን የጀመረው ሐምሌ 12 1966ዓም ነው።ኮሚስዮኑ ሥራውን በጀመረ በወሩ የመጀመርያውን የሥራ አፈጻጸሙን ሪፖርት ያሰማው ነሐሴ 21 ቀን 1966 ዓም በአዋጁ ላይ ከተገለጹት ለአንዱ ለህዝብ ብቻ ነው።ለንጉሰ ነገሥቱና ለፓርላማው ጽ/ቤት(ፓርላማው በዚህ ወቅት እረፍት ላይ ስለሆነ) ይህንን ሪፖርት አላቀረበም።[82]

እንድያውም ኮምስዮኑ ስራውን እንደጀመረ እና <u>ገና ደርግ አስተባባሪ ኮሚቴ</u> እያለ፤ ኮሚስዮኑን ያቋቋመውም ፓርላማ ሳይፈርስ ፤ ህገ መንግስቱም ሳይታገድ ፤ ንጉሰ ነገሥቱም ከዙፋናቸው ሳይወርዱ ፤ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም እና ዶ/ር በረከት ሀብተስላሴ የኮሚስዮኑን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለአስተባባሪው <u>ደርግ</u> ያቀርቡም ውይይትም ያደርጉ ነበር።[83]

ከአስተባባሪው ደርግ ጋር ያደርጉት የነበረው ውይይት ዓላማም ንጉሱን ለማውረድ ኮሚስዮኑን መቀስቀሻ እንዲሆን ማድረግ ነበር፤ ይሁንና ሁለቱም የኮሚስዮኑ አባላት ንጉሱን ለማውረድ የኮሚስዮኑ ውጤት አስፈላጊ እንዳልሆነ ፣ ህገ መንግስቱ ወረቀት ስለመሆኑ፤ ጠመንጃው ያለውም በእጃችሁ ስለሆነ ይልቁንም “ጊዜ በወሰደና በቆየ ቁጥር ከፍ ያለ አደጋን ሊያስከትል ስለሚችል ንጉሱን ባስቸኳይ ማውረድ አለባችሁ”

---

[81] ይድረስ ለባለታሪኩ 2010 ገጽ219 ተስፋዬ መኮንን

[82] ወንበር የዓለማየሁ ኃይሌ መታሰብያ ድርጅት ፔሮዲካል የ1966ቱ መርማሪ ኮሚስዮን አነሳስ ከንውን እና ከዝያ የቀመስነው ገጽ 19 በዛወርቅ

[83] አብዮቱና ትዝታዬ ገጽ 127 ሌተና ኮለኔል ፍስሐ ደስታ

በማለት በተለይ ከዶ/ር በረከት ሀብተስላሴ ምክር እንደተሰጣቸው ሌተና ኮሎኔል ፍስሀ ደስታ ነግረውናል።[84]

ደርግ መንግስት ከሆነ በኋላ በሰላም እጃቸውን ሰጥተው በቁጥጥር ስር በነበሩት የቀድሞ ባለስልጣኖች ላይ የግድያውን እርምጃ እንዲወስድ የኮሚስዮኑ ሊቀመንበር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም እና የኮሚስዮኑ ሌላው ዋነኛ ተዋናይ ዶ/ር በረከት ሀብተስላሴ ይገፋፉ እና ይመከሩ እንደነበር የነፍሰ ገዳዩ መንግስት መሪ ጨካኙ ኮለኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ጠቁመዋል።[85]

የመጀመርያውን የሥራ አፈጻጸሙን ሪፖርት እንኳን በአዋጁ ድንጋጌ መሰረት ለንጉሰነገሥቱና ለፓርላማው ጽ/ቤት ኮሚስዮኑ ያለማቅረቡ ፣ በኋላም ከላይ የተገለጸው ከአስተባባሪው ኮሚቴ ጋር የነበረው ምክክር እና የሥራ ቅርርብ የሚያስረዳው ፣ ኮሚስዮኑ እንደህዝቡ በሥርአቱ ላይ እንደ አመጸ እና ጡንቻውን እያፈረጠመ ወደ ሥልጠን እርከን ለመውጣት ከፍተኛ የታሪክ እሽቅድምድም ላይ ከነበረው ወታደራዊ ኃይልም ጋር የሥራ ግንኙነት መፍጠሩን ነው።ይህ የሥራ አፈጻጸም ወገንተኛነትን ያሳያል ቃለመሃላውም መሻሩን ያመላክታል።

## 5.9 የኮሚስዮኑ የሥራ ዘመን

ኮሚስዮኑ የተሰጡትን ሥልጣንና ኃላፊነት ይዞ የሚቆየው ለሁለት አመት ብቻ ነው።ይሄውም አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከሰኔ 8 ቀን 1966 ዓም እስከ ሰኔ 8 ቀን 1968 ዓም ድረስ መሆኑ ነው።[86]

ከሁለት ዓመት ቆይታው በኋላ የኮሚስዮኑ መኖር አስፈላጊ ከሆነ ፣ የሚቆይበት የሥራ ዘመን በፓርላማው ይወሰናል።[87] ይሁን እና ፓርላማው መስከረም 2 ቀን 1967 ዓም ከንጉሰነገሥቱ ሥልጣን መውረድ ጋር ተያይዞ ተበትኗል።ወታደራዊ መንግስትም አዋጅ አውጥቶ ከሁለት ዓመት በላይ መቆየት የሚያስችለውን ህጋዊ አቅም ለኮሚሲዮኑ አልሰጠውም።

ከሁለት ዓመት በላይ የሚያቆየውን የህግ ድጋፍ ሳያገኝ ከህግ ውጭ ማለት ይቻላል ፤ ስራውን ያቆመው እስከ 1969 ዓም መጨረሻ ድረስ ቆይቶ ነው።[88]

---

84 ዝኒ ከማሁ

85 የሌተና ኮለኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም ትዝታዎች ገጽ147-148 ከገነት አየለ አንበሴ

86 አዋጅ 326/66 አንቀጽ3(1)

87 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ3(4)

88 የእስር ቤቱ አበሳ አቶ አበራ ጀምበሬ ገጽ 43

ከፍርሀት በመነጨ ዝምታ ይሁን ፣ ወይም ለተፈጸመው ከፉ ተግባር ተጋሪ በመሆን፣ ወይም ለግፍ እርምጃው ሁሉ ይሁንታ ለመስጠት ለመቻል ይሁን ከሰኔ 8 ቀን 1968 ዓም በኋላ ከህግ ውጭ ኮሚስዮኑን ይዘው አባላቱ ቆይተዋል።

ስለዚህም ከሰኔ 8 ቀን 1968 ዓም  ኮሚስዮኑ እስከፈረሰበት 1969 ዓም መጨረሻ ድረስ ኮሚስዮኑ የሰራው ሁሉ ከአቋቋመው አዋጅ ውጭ በመሆኑ ህገወጥ ነው።

## 6 ማጠቃለያ

ከላይ በዝርዝ እንደተገለጸው አዋጁ ያስፈጽማቸዋል የተባሉት ዋነኛ ዓላማዎች ባለስልጣናት ሥራቸውን እና አገራቸውን በቅን ልቦና እና በትክክል የማከናወን ግዴታ መፈጸም ወይም አለመፈጸማቸውን መመርመር፣እንዲሁም በመንግስት ላይ የህዝብ እምነት እንዲሰፋ ማድረግ እና የመንግስት ባለስልጣኖችም ሊኖራቸው የሚገባው ከፍተኛ ታማኝነት መኖር አስፈላጊ መሆኑን ማረጋገጥ ነበር።[89]ይሁንና ኮሚስዮኑ ይህንን ኃላፊነቱን ከላይ በዝርዝር በተገለጸው የሥራ አፈጻጸም ምክንያት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ።

ህዳር 14 1967 ዓም በደርግ ለተወሰደው የግፍ እርምጃ ኮምስዮኑ የሰጠውን የበኩሉን አስተዋጽኦ አጉልቶ የሚያወጣው ኮምስዮኑ ከሐምሌ 12 1966 ዓም እስከ ህዳር 13 1967 ዓም ድረስ ምርመራውን የአካሄደበት፣የስራ አፈጻጸሙም ሆነ በመጨረሻም ከላይ የተገለጸውን የምርመራ ውጤቱን ያስረከበበት ስርአት በአቋቋመው አዋጅ ቁጥር 326/66 መሰረት ያለመሆኑ ነው።

በዚህ ምክንያት ኃላፊነታቸውን በመዘንጋት ያለአገባብ በስልጣን የተጠቀሙ ፣ታማኝነት የጎደላቸውን፣ በዳኝነት እና በአስተዳደር በደል ያደረሱ የቀድሞቹ ባለስልጣኖቹ አጥፊ መሆን ወይም አለመሆናቸው በፍርድ ሂደት ውስጥ አልፎ ተለይቶ እንዲታወቅ ባለመደረጉ ጥፋተኝነታቸው ሲረጋገጥ በህግ እንዲቀጡ የማድረጉ የፍርድ ሂደት ሳይፈጸም ቀረ ።

አዋጁም ያስፈጽማቸዋል የተባሉት የሰብአዊ መብት ጥበቃ እና የህግ የበላይነት የሚገለጥበት አጥፊ የሆኑት ተለይተው የሚታወቁበት የፍርድ ሂደት እንዳይከናወን በመደረጉ አገር ከፍርድ ሂደቱ የሚያገኘው መጠነ ሰፊ ጥቅም ሙሉ ለሙሉ ከሸፈ።

ባለስልጣኖቹ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ሳይታይ፣ ከፍርድ ውጭም በአስከፊ ጭካኔ ስለተገደሉ ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ በግፍ የተገደለ ሁሉ ሊያገኝ የሚገባውን የሰማዕታትነቱን ማዕረግ እና ጸጋ ተጎናጽፈውታል። ሃውልትም እየቆመላቸው ነው።ገድላቸውም እየተዘከረ ነው። በአስተዳደር በደል እና በተፈጥሮ ሕግ

---

[89] አዋጅ 326/66 መግቢያ ፓራግራፍ 2

መዛባት ምክንያት የችጋሩ ሰለባ የሆኑትም የወሎ ረሃብተኞች ዕልቂት ጉዳይ ዳዋ ለብሶ እንዲቀር አድርጓል።

እንዲሁም ወደፊት ሊፈጠር ስለሚችለውም ተመሳሳይ የአስተዳደር በደል ከልከላ የሚያደርግ ምሳሌ፣ አገር ይህን ታሪካዊ አጋጣሚ ምክንያት አድርጎ እንዳይፈጥር የኮሚስዮኑ ገለልተኛ ያልሆነው የሥራ አፈጻጸሙ እና የደርግ አስከፊ እርምጃ እንቅፋት ሆነ።

ሕዳር 14 1967 ዓም በተወሰደው አረመናዊ ጭፍጨፋ ፣ በሀገሪቱ እስከ አሁን በተከታታይ ለተፈጸሙት የሰብአዊ መብት ጥሰት እና ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ "የፖለቲካ ውሳኔ" በሚል በደርግ እና በሌሎች የወቅቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣እንቅስቃሴዎች እና ቡድኖች ለተወሰዱ አስከፊ እርምጃዎች ሁሉ የመጀመርያውን ምዕራፍ በመከፈት ለአገራችን የፍጅት ታሪክ ቀዳሚ እርምጃም ሆነ።

ከላይ እንደተገለጸው የኮሎኔል የዓለም ዘውድ የጦር ኃይሎች ኮሚቴ እና የመርማሪ ኮሚሲዮን ምንም እንኳን የተቋቋሙበት ድብቅ ዓላማው ለክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን መንግስት እድሜ ማርዘም ቢሆንም ፣የጦር ኃይሎች ኮሚቴ ለደርግ መፈጠር እና መደራጀት እንዲሁም የመርማሪ ኮሚሲዮኑ የሥራ አፈጻጸም ደግሞ ለደርግ መጠናከር የሚረዱትን ከፉ ድርጊቶች ሁሉ እነዚህ ሁለት ቡድኖች ፈጽመዋል።

በተጨማሪም የምርመራው አፈጻጸም እና መዘዙ የዴሞክራሲ ኃይሎችን ሁሉ ንቆ ጠልቶና አግልሎ ሥልጣኑን በብቸኝነት እንዲቆናጠጥ ለደርጉ የልብ ልብ ሰጥቶታል።

በዚህ ህገ ወጥ ድርጊቱ ኮለኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እና ሌተና ኮሎኔል ፍስሀ ደስታ እንዳጋለጡት እና እንደጠቆሙበት ኮምስዮኑ ራሱን በቀጥታ ለንጉሱነገሥቱ ከዙፋናቸው መውረድ መቀስቀሻ ለተወሰደውም ለዚያ አስከፊ የግፍ እርምጃም በማወቅም ይሁን ባለማወቅ መሳርያ አላአደረገም ማለት አይቻልም።

የዚህም ህገ ወጥ የስራ አፈጻጸም ውጤት በስልጣን ላይ ለመቆናጠጥ እና ምንም ለማድረግ ለተዘጋጀ አምባገነን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አግዟል። ለግፍ እርምጃውም አቅም መሰጠቱ እና መገፋፋቱ አሌ የማይባል ዕውነት ነው።

ይህ የኮሚስዮኑ የስራ አፈጻጸም በወቅቱ ይህን ውጤት አያመጣም ፣ ውጤቱ ይህ እንዲሆንም ሆን ብለው የሰሩ የኮምሲዮኑ አባል የሆኑ የሉም ብለው የሚያምኑ ካሉ እራሳቸውን ለሌላ ለከፋ ተግባር እያዘጋጁ እንዳይሆን እፈራለሁ።

ኮሚሲዮኑ የሰራው ህገ ወጥ ሥራም ሀገሪቱ እስከዛሬ የግፍ ታሪኳን ካደለቡት ክፉ ስራዎች መሀል አንዱ መሆኑ ጮክ ተብሎ አልተነገረም።አለመነገሩም ፣ የኮሚሲዮኑ አባላት አለመወቀሳቸውም፣ ይቅርታም በግልም ይሁን በቡድን አለመጠየቃቸው የአበሳ ዘመናችን ቶሎ እንዳያልቅ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል።

"በትክክለኛነታቸው እና በኀሊናቸው ንጽህና ብርቅ የሆኑት"[90] የኮምስዮኑ አባላት በአዋጅ በተሰጣቸው ኃላፊነት መሰረት በምርመራቸው ውጤት መሰረት ሊከሰሱ ይገባል ከአሉአቸው 39 ሰዎች መሃል የአንዱን ብቻ ፍርድ ቤት መቅረቡን ሲገልጹ[91] የሌሎቹን ዕጣ ፈንታ ግን በሪፖርቱ ላይ እንኳን ደፍረው አላሳዩንም።

ህዳር 14 1967 ዓም ይህ የግፍ እርምጃ በስድሳዎቹ ላይ ሲወሰድ ፕሮፌሰር መስፍን አእምሮአቸው ተበጥብጦ ለአስራ አምስት ቀናት የኮሚስዮኑን ሥራ አቋርጠው ከቤት ሳይወጡ መቆየታቸውን እንደትልቅ ጀብድ አድርገው ነግረውናል።[92]

ሊሆን የሚገባው በግፍ የተገደሉት ኮሚስዮኑ የመረመራቸውና ወደፊትም በሌላ ጭብጥ የሚመረመሩ የቀድሞ ባለሥልጣኖች በመሆናቸው፣ እንዲሁም ኮሚስዮኑ ልዩ በሆነ ታሪካዊ ምክንያት ብሄራዊ ችግር ለመፍታት በ ብሄራዊ ምክር ቤቱ የተቋቋመ ስለሆነ፤ ከዚህ በላይ በተገለጸው ቀን የግፍ እርምጃው ሲወሰድ ፣ ሲሆን ሁሉም የኮሚስዮኑ አባላት በሙሉ በአንድ ላይ፤ አለበለዚያም ለህግ የበላይነት ተቆርቋሪ ነኝ የሚል የኮሚስዮኑ አባል ከኮሚሲዮኑ አባልነት በአዋጅ 326/66 አንቀጽ 3(5) መሰረት ወድያውኑ ሥራውን ለቆ መውጣት ይገባው ነበር።

ይህ ሆኖ ቢሆን ኖሮ እርግጥ ነው ሥራውን በሚለቀው አባል ወይም አባሎች ላይ አደጋ ያንዣብብ ይሆናል።ይሁንና የህግ የበላይነትን ለማጎልበት ለሚደረገው እርምጃ የመጀመርያውን ወሳኝ ምዕራፍ ይከፍት ነበር።መስዋዕትነቱም የመንፈስ እና የሲቪል ጀግንነትንም ያጎናጽፍ ነበር። ኮሚስዮኑም ልዩ በሆነ ታሪካዊ ሁኔታ የተቋቋመበትን ብሄራዊ ዓላማም ያስከብር ነበር። የሆነው ግን የአስራ አምስት ቀን ኩርፍያ ነው።በነገራችን ላይ የነገሩን እውነት ከሆነ ይህችንም ታከል ተገኘ የተባለው እኮ ከፕሮፌሰር መስፍን እንጂ ከሌሎቹ የኮሚስዮኑ አባላትማ ምንም የተሰማም ነገር የለም።

እንዲያውም ካልጠፉ ቀን የግፍ እርምጃው በተወሰደበት ቀን ህዳር 14 ቀን 1967 ዓም በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በተያዙት ሌሎቹ የመንግስት ባለስልጣኖች ላይ ለሚደረገው ምርመራ እንዲያግዝ ፣

---

[90] አገቱኒ ተምረን ወጣን መስፍን ወ/ማርያምአዲስ ገጽ 12 አዲስ አበባ 2002
[91] የመርማሪ ኮሚሽን ሪፖርት ገጽ33
[92] እንዘጭ እምቦጭ መስፍን ወልደ ማርያምገጽ 128

ህዝቡ የበደሉን አቤቱታ ለኮሚስዮኑ እንዲያቀርብ በመገናኛ ዘዴዎች ለህዝብ ማሳሳብያ እንዲተላለፈ ኮሚስዮኑ አደረገ።[93]

የኮሚስዮኑ ቃለ ጉባኤዎች እንደሚያስረዱት ሁሉም አባሎች በአንዳንድ እክል ምክንያት አንዳንድ ቀን ከጉባኤው ከመቅረት ውጭ ስራቸውን ያቋረጡ የሉም ብሎ መደምደም ይቻላል።

IESMS መለያ ቁጥሩ 1947 በሚል በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተመዝግቦ የሚገኘው የሰኔ 18 ቀን 1967 ዓም 53ኛው ቃለ ጉባኤ (ተመርማሪዎቹ በግፍ ከተገደሉ ስድስት ወር በኋላ መሆኑ ነው) አቶ ሽብሩ ወልዴ የተባሉ በአቶ ታፈሰ ሀብተሥላሴ የቱሪስት ድርጅት ዋና ሥራአስኪያጅ ላይ የአቀረቡትን አቤቱታ ምክንያት በማድረግ በተከናወነው ምርመራ ላይ ሊቀመንበሩ ኮማንደር ለማ ጉተማ በጉንፋን ምክንያት ድምጻቸው ተዘግቶ ስለነበር በውክልና ጉባኤውን የመሩት ፕሮፌሰር መስፍን ናቸው።

ከዚህ በላይ ከተገለጹት ቃለጉባኤዎች በተጨማሪ በኮማንደር ለማ ጉተማ ፊርማ በ1968 ዓም የመጀመርያዎቹ ወራት አካባቢ የወጣው የኮሚስዮኑ ሪፖርትም የሚያሳየው ከአስራ አምስት ቀን ኩርፍያ በኋላም ፕሮፌሰር መስፍን ከሌሎቹ የኮሚስዮኑ አባላት ጋር በመሆን ኮሽታም ሳያሰሙ ራሳቸውንም ሆነ ኮምስዮኑን ተራ መርማሪ አድርገው ምርመራውን ማጧጧፉን እንደተያያዙት መዝለቃቸውን ነው።[94]

የኮሚስዮኑ አባላት ምንም አይነት እርምጃ ባለመውሰዳቸው ከአራት ዓመት የእስር ስቃይ በኋላ ሌሎች የኮምስዮኑ ተመርማሪ የነበሩ በ1971 ዓም እንደገና በደርግ በግፍ ተገደሉ።እነሱም ክቡር ጸሃፊ ትዕዛዝ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ፣ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመ ሥላሴ፣ክቡር ደጃዝማች ካሣ ወልደማርያም ናቸው።[95]

እነዚሁ "በትክክለኛነታቸው እና በኅሊናቸው ንጽህና ብርቅ የሆኑት"[96] የኮምስዮኑ አባላት ተመርማሪዎቻቸው በፍርድ ቤት ጉዳያቸው የመታየት ዕድል እንዳያገኙ ተደርጎ በግፍ ግድያ ሲፈጸምባቸው እና ይህን አረመኔያዊ ድርጊት ህጋዊ ለማድረግ ደርግ ሲፎክር በግልም ይሁን በቡድን በአደባባይ ወጥተው በወቅቱም ይሁን በኋላ ለሌላው ህብረተሰብም አርአያ በመሆን ይህን አስከፊ ጥፋት ለማውገዝ የመንፈስ አቅም አጡ።

ደርግን በዚህ አስከፊ ሥራው የኮምስዮኑ አባላት በግልም ይሁን በቡድን ጮክ ብለው በአደባባይ ወጥተው ያላወገዙት ፣ ያልታገሉት ለሰራው ክፉ ተግባር ሁሉ የሚገባውን በወቅቱ ያላደረጉት፣ ምንም ያላሉት፣

[93] የመርማሪ ኮሚስዮን ሪፖርት ገጽ 32
[94] የመርማሪ ኮሚስዮን ሪፖርት ገጽ 56
[95] የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድቤት ም/ቁ/ል/ዐ/ም/መ/ቁ/401/85ገጽ39
[96] አገቱኒ ተምረን ወጣን መስፍን ወ/ማርያምአዲስ ገጽ 12 አዲስ አበባ 2002

ለተፈጸመው ክፉ ተግባር ፣ የኮሚስዮኑ የስራ አፈጻጸም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተጋሪ ስለአደረጋቸው ይሆን ብሎ መጠየቅ ይገባል እላለሁ።

የደርግ አገዛዝ የበላይ ሹማምንት ዛሬ እንደሚነግሩን [97] እሰይ አበጀህ በሚል የውስጥ ለውስጥ ድጋፍ ለግፈኛው ሲያጎናጽፉት ቆይተው ፣ በአባላቱ በራሳቸው በተረቀቀው አዋጅ[98] መሰረት ተልዕኮውን በድል እንደአጠናቀቀ መልዕከተኛ ፣ ከህግ ውጭ ከአንድ አመት በላይ የቆየው ኮሚስዮን ፈረሰ ተባለ።

ከዚህ በላይ በዝርዝር የገለጽኩት መጠነ ሰፊ የሆነው የኮሚስዮኑ የሥራ አፈጻጸም ችግር ኮሚስዮኑ ምን ያህል ከአቋቋመው እና ስራውን ሊያከናውንበት ከሚገባው ህግ በተጻራሪ መቆሙን ያሳያል።

ኮሚስዮኑ የ1965 ዓም የወሎ ረሃብና ዕልቂት ጋር ጉዳያቸው የተያያዘውን ባለስልጣኖችን ሲመረምር ነሃሴ 28 ቀን 1966 ዓም በ 13 ኛው ቃለ ጉባኤ የወቅቱን የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አዘጋጅ የነበሩትን አቶ በዓሉ ግርማን መርምሯል።በዚህም ምርመራው የህሊና ደወል በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሀፋቸው ላይ ያለውን “ሐስ” የተባለውን ገጸ ባህርይ ከአቅሙ በላይ ይታገል እንደነበር ፕሮፌሰር መስፍን አስገንዝበዋቸው፣ ገጸ ባህርዩ ላይ የሚከናውኑትን ተግባሮች ያምኑበት እንደሆነ[99] ጠይቀዋቸዋል።

ከዚሁ ጋር በማያያዝም ስለ ወሎ ችግር የዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች ያሱሙትን ጩኸት እና ያሳዩትትን የፎቶግራፍ ትርኢት፣ ተማሪዎቹ የሰዉትን ቁርስ፣ ቴሌኮሚኒኬሽን የለገሰውን ዘጠና ሺህ ብር አስታውሰውአቸው፣ የወሎን የችግሩን መጠን እንዴት አላወቅም ሊሉ ይችላሉ[100] ሲሉ ጥያቄ በመጠየቅ ኃላፊነታቸውን መወጣት መቻል ያለመቻላቸውን እንዲመረምሩ አድርገዋል።

የኢትዮጵያ የሄራልድ ጋዜጣ አዘጋጅን አቶ ተሥፋዬ ካብትህይመርን ኮሚስዮኑ አስቀርቦ በመረመረበት ወቅትም ፣ፕሮፌሰር መስፍን እኒህን ተመርማሪ ፣ጋዜጠኛ ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያዊ ከሁሉም በላይ ሰው መሆናቸውን ከነገሩአቸው በኋላ፣ እርሳቸው ምስክር የሆኑበት እልቂት ሲፈጸም እያዩ እንዴት የሚኒስትሩ የቃል ትዕዛዝ ከሕግ ውጭ መሆኑን ለማስረዳት አልገፉበትም[101] ሲሉ ከሙያቸው የሚመነጨውን ኃላፊነታቸውን አስረድተዋቸዋል።

ከዚህ የምርመራ ሂደት የተገነዘብኩት እነዚህ ጋዜጠኞች በመንግሥት የተጣለባቸውን ተጽእኖ ሁሉ ተቋቁመው፣ በወቅቱ ከፊታቸው የተደቀነውን አስከፊ እልቂት በማጋለጥ የችጋሩ ሰለባ የሆነው ህዝብ

---

97 የሌተና ኮለኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም ትዝታዎች ገጽ147-148 ከገነት አየለ አንበሴ

98 አገቱኒ ተምረን ወጣን አዲስ አበባ ገጽ13

99 የመርማሪ ኮሚስዮን ቃለ ጉባኤ11 — 20 ገጽ 2 IESMS መለያ ቁጥር 1945

100 የመርማሪ ኮሚስዮን ቃለ ጉባኤ11 — 20 ገጽ 3 IESMS መለያ ቁጥር 1945

101 ዝኒ ከማሁ ገጽ 5

ሊድን የሚችልበትን ሁኔታ ሊያመቻቹ ይገባ እንደነበር ፕሮፌሰር መስፍን አጥብቀው በመንገር ኃላፊነታቸውን መወጣት መቻል አለመቻላቸውን እንዲመረምሩ ጋዜጠኞቹን በምርመራው ላይ እንዳሉ ያሳስብዋቸው መሆኑን ነው። በዕርግጥ ይህ መንፈስን የሚመረምር ማስገንዘብያ ለጋዜጠኞቹ መቅረቡ የሚገባ ነበር።

እኔም ዛሬ ይህን የማነሳው ፕሮፌሰር መስፍን የኮሚስዮኑ ተመርማሪዎች በግፍ እስከተገደሉበት ድረስም የኮሚስዮኑ አባል እና ዋና ተዋናይ ስለነበሩ ይህን <u>ኃላፊነታቸውን በኢትዮጵያዊነታቸው እና ከሁሉም በላይ ሰው በመሆናቸው</u> የስራ አፈጻጸማቸው ኮሚስዮኑን ከአቋቋመው ህግ ውጭ እንዳይሆን ፣ እንዲሁም ከ1965ቱ ዓም የወሎ ረሃብና ዕልቂት ጋር ጉዳያቸው የተያያዘ ባለስልጣኖች ምርመራ ውጤት በፍርድ ቤት እንዲታይ የሚያስችለውን ሁሉ ማድረግ ነበረባቸው።

ተመርማሪዎቹም በግፍ ሲገደሉ ከኩርፍያ የዘለለ ጠንከር ያለ እርምጃ በመውሰድ የደርግን መንግሥት ሊታገሉት ይገባ ነበር። ይሁንና አላደረጉም። ስለዚህም እሳቸውም የሥራ አፈጻጸማቸውን <u>ሰው እና ኢትዮጵያዊ</u> ስለሆኑ ከዚህ በላይ ስማቸው እንደተገለጸው ጋዜጠኞቹ ሊመረምሩ ይገባል እላለሁ።በዚህ የስራ አፈጻጸም ጥሰት ምክንያት ከላይ እንደአሳየሁት አገር ተጎድቷል። ፕሮፌሰር መስፍን ግን ይህ የሥራ አፈጻጸማቸው ትንሽም ጉድፍ እንደማይገኝበት እርግጠኛ መሆናቸውን ገልጸዋል።[102]

የኮሚስዮኑን የሥራ አፈጻጸም ለማጣራት ሌላ መርማሪ ኮሚስዮን በአዋጅ መቋቋም የለበትም።ይሁንና አባላቱ ለሥራ አፈጻጸማቸው እና ስለውጤቱ ብዙ እየተባሉ ላለፉት አርባ ዓመታት መቆየቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከላይ በዝርዝር ስለአነሳሁአቸው የህግ እና የፍሬ ነገር ጭብጦች ሊነግሩን ይገባል ብዬ ኣምናለሁ።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የአገራችን ስመጥር ጸረ ፋሺስት አርበኞቻችን በጣልያን እና በሌሎች አገሮች የፋሺስት ኢጣልያ ግዞተኞችና እና እስረኞች ሆነው በነበሩበት ዘመን ለቀለብ ይቆረጥላቸው የነበረውን ወርሃዊ ገንዘብ ለጣልያን መንግሥት በባንዳነት አድረው ለሙሶሎኒ ያገለግሉ ከነበሩት ደመወዝተኞች ጋር ደምረው የፋሺስት ጣልያን ደመወዝተኞች በሚል የሥም ዝርዝራቸውን በአንድ አርስት ስር ፣በአንድ ላይ በመጻፍ የአገራችንን ስመ ጥር ጸረ ፋሺስት አርበኞቻችን ስም አጉድፈዋል።[103]ይህ ሆን ተብሎ የተፈጸመ ከፉ ተግባራቸው ሰው በአገር እንደአልወጣ በማስመሰሉ ብዙ ሰው ተስፋ አስቆርጠዋል፣ አበሳጭተዋል። በሌላ በኩልም በአገራችን የተራማጅ ኃይሎች በደርግ ላይ ያደረጉትን ትግል እስከ አሁን ያለምንም ርህራሄ ያወግዛሉ።

---

[102] አገቱኒ ተምረን ወጣን መስፍን ወ/ማርያም አዲስ ገጽ 11 አዲስ አበባ 2002

[103] አዳፍኔ ፍርሃትና መከሸፍ መስፍን ወ/ማርያም ገጽ 151 አዲስ አበባ 2007

ለቀድሞ የደርግ ባለስልጣኖች በፍርድ ቤት ለቀረበባቸው ክስ ሶስተኛ ተከላካይ ምስክር[104] በመሆንም ለደርግ ስርአት የነበራቸውን ቀረቤታ ሲያሳዩን የተራማጅ ኃይሉን ታሪኩንም ሆነ መስዋእትነቱንም ዋጋ ቢስ ለማድረግ በፍርድ ቤቱ ውሎአቸው ክፉኛ ደከመዋል። ይህም ዘመቻቸው ላለፉት አርባ ዓመታት ቆይቷል።

ይህንን ሁሉ ያነሳሁት ስመጥር ጸረ ፋሺስት አርበኞቻችንንም ሆነ ሲቪል ጀግኖቻችንን እንዲሁም የተራማጅ ኃይሎችን ታሪክ ለማጉደፍ ኃላፊነት የጎደለው ሥራ መስራታቸውን ለማስታወስ ብቻ ሳይሆን የቆየ ታሪክ ለማንሳት እና ለመከራከር እንደሚቻል ይህ የከፋት ስራቸው ለእኔ አቅም እንደሰጠኝ ለማስገንዘብ ነው።

የደርግ የአገዛዝ ዘመን በጣም የሚያስፈራ፣ ማንነትን የሚፈታተን መሆኑን በወቅቱ ወጣትም ብሆን የምገነዘበው ነው። ይሁንና ዘመኑ በሌላ ዘመን ሲሻር በዚያን ጊዜ የተፈጠረን የህሊናን ቁስል በንስሀ ማጥራት ለአገር የብሄራዊ እርቅን ምዕራፍ ይከፍታል ፤ ለራስም መንፈሳዊ አቅምን ያመጣ ይሆናል ብዬ በመጨነቅ ነው ይህን ጉዳይ ያነሳሁት።

ያ ዘመን በሌላ ዘመን ሲተካ የማየት ዕድሉን አግኝተው ፣ ይህንንም ዘመን የኖሩት የዕድሜ ባለጸጎች የኮሚስዮኑ ተዋናዮች ፣ አይ አሁንስ ድብብቆሹ እና ፉከራው ይብቃ ብለው እውነቱን እንዲነግሩን ፣ እንዲያስተምሩን ለመገፋፋት እንጅ ለፍርድ ለማቅረብም አይደለም።ምናልባትም የመጨረሻ ዘመናቸውን ለማሳመር እና ጉዞአቸውንም ክብር የተሞላው ለማድረግ ማገዜ ነው።

ስለዚህም ይህ ጉዳይ ከአርባ ዓመት በላይ ቢሆነውም የይቅርታ ጥያቄ ይርጋ የለውም እና በህይወት ያሉት የኮሚስዮኑ አባላት ከዚህ በላይ የዘረዘርኩአቸውን የፍሬ ነገሮች እና የአዋጁን አንቀጾች መሰረት አድርጌ ያቀረብኩት የህግ አስተያየት፣ ፉከራቸው ባዶ እንደሆነ አስገንዝቦአቸው፣መንፈሳዊ አቅምም ሰጥቶአቸው፣ ከአፈርኩ አይመልሰኝ ከሚለውም ኃላፊነት ከጎደለው ክርክርም ነጻ አውጥቶአቸው፣ እውነቱንም ይነግሩናል አገርንም ይቅርታ ይጠይቁ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ ጉዳይ ከዚህ በበለጠ ትኩረት አግኝቶ ቢመረመርም ይበልጥ ለአገር የሚበጅ ትምህርት ይገኛል እላለሁ።

[104] ልዩ አቃቤ ህግ በእነ ኮለኔል መንግስቱ ኃይለ ማርያም ላይ ያቀረበው ክስ መዝገብ ቁጥር ል/0/ም/መ/ቁ/401 /85 ገጽ ፲5